# በኢፌዲሪ የፍትሕ ሚኒስቴር በቀረበው የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ረቂቅ አዋጅ ላይ ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የቀረበ አስተያየት

(ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ/ም)

## በረቂቅ አዋጁ ድንጋጌዎች ላይ የቀረቡ ዝርዝር አስተያየቶች

### 1. የረቂቅ አዋጁ መግቢያ

ይህ ክፍል በተለምዶ አንድን ሕግ ለማውጣት ያስፈለገበት ምክንያት የሚገለፅበት ነው፡፡ ስለሆነም የህጉ መነሻ የሆኑ የፖሊሲ ታሳቢዎች፤ ሕገመንግስታዊ ጥበቃ የሚደረግላቸው መብቶች ወይም የአለም አቀፍ ሕግ ግዴታዎች በመግቢያው ውስጥ እንደሚቀመጡ ይጠበቃል፡፡

1. ፓራግራፍ 1፡- ይህ ሕግ የሚወጣው በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ ነን በምንልበት ወቅት እንደመሆኑ የዚህ ፓራግራፍ ይዘት በንጉሱ ዘመን በ1960ዎቹ ማህበራትን በተመለከተ የወጡትን ህግጋትና ደንቦች በማሻሻል እና ክፍተቶችን በመሙላት መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች አመቺ የሕግ ማዕቀፍ መፍጠር ላይ ማተኮር ሲገባው ይበልጥ ትኩረቱን ያደረገው የቁጥጥር አስፈላጊነት ላይ ነው፡፡
2. ፓራግራፍ 2፡- ይህ ፓራግራፍ ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን እንዲጠቀሙ ማስቻል አስፈላጊ ለመሆኑ አወንታዊ እውቅና መስጠቱ አግባብ ነው፡፡ ሆኖም በዚህ መብት ለመጠቀምና መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ነፃ እንቅስቃሴ በእኩል ደረጃ ወሳኝ የሆኑት የመሰብሰብ እና ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብቶችም በመግቢያው ውስጥ መጠቀስ ነበረባቸው፡፡
3. ፓራግራፍ 3፡- ይህ ፓራግራፍ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት በሕገ-ወጥ ተግባራት ላይ እንደሚሳተፉና መንግስት የሕዝቡን ጥቅም ለመጠበቅ በቅርበት ሊከታተላቸውና ሊቆጣጠራቸው እንደሚገባ ግምት የወሰደ ይመስላል፡፡ ይህም ረቂቁ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ሕግ ከመሆን ይልቅ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ባህሪ ያለው አስመስሎታል፡፡ ረቂቅ ሕጉ ይበልጥ ያተኮረው በቁጥጥርና ቅጣት ላይ ከመሆኑም በላይ ህጉ በመንግስት ቁጥጥር የማይደረግበት የተደራጀ እንቅስቃሴ ሁሉ ወንጀል እንደሆነ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማሕበራት በፈቃደኝነት /volunteerism/ እና በኃላፊነት መንፈስ ሕዝብን ለመጥቀም ተቋቁመው ሚሊዮኖችን የሚያገለግሉ መሆናቸው ታስቦ እምነት ሊጣልባቸው ሲገባ ህጉ ከዚህ ይልቅ ከጥርጣሬ በመነሳት ስራዎቻቸውንና ሀብቶቻቸውን በመቆጣጠር እና በመቅጣት ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡
4. ፓራግራፍ 4፡- ይህ ፓራግራፍ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ልማታዊ ሚና እንዳላቸው እና በዚህም ረገድ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው እውቅና ይሰጣል፡፡ ሆኖም ግን የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ያላቸውን ሚና አላካተተም፡፡ ለሲቪል

ማህበረሰብ ተቋማት ልማታዊ ሚና የሚደረገው ድጋፍም ቢሆን በረቂቅ ሕጉ ቀሪ አንቀጾች ላይ በግልጽ አልተንፀባረቀም::

> **የማሻሻያ ሀሳብ:-** የረቂቅ ህጉ በቡድን የተደራጁ ዜጎች መብቶቻቸውን በተሟላ መልኩ ለመጠቀም እንዲችሉ፣ በልማትና በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ለመሳተፍና አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችሉ፣ በማሕበራዊ ህይወታቸው ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ባሕል እንዲያዳብሩ እና ለህዝቡና ለሚወክሉት የህብረተሰብ ክፍል ተጠያቂነታቸውን ለማረጋገጥ አመቺ የሕግ መአቀፍ በመፍጠር ላይ ትኩረት በመስጠት በመግቢያው በአወንታዊ አገላለፅ ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል::

**2. የቃላት ትርጓሜዎች (አንቀጽ 2)**

**የበጀት ዓመት**

**አንቀጽ 2/2:-** የበጀት አመቱ በኢትዮጵያ እና በጎርጎሮሳዊያን አቆጣጠር መቀመጡ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ለገንዘብ አያያዝ ስርዓትና ለሪፖርት አቀራረብ አንደኛውን መርጠው እንዲጠቀሙ ዕድል ስለሚሰጥ አግባብነት ያለው ነው::

**የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ትርጓሜ**

**አንቀጽ 2/3:** የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከውጭ ሊሰበስቡ የሚችሉትን የገንዘብ መጠን በ10 በመቶ ይወስናል:: ከዚህ የበለጠ ገቢ ከውጭ የሚያገኙ ከሆነ እንደ ውጭ ድርጅት ወይም ማህበር የሚታዩ ይሆናል:: ይህ አንቀጽ ከታች በተዘረዘሩት ምክንያቶች በአብዛኞቹ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ህልውና እና እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጫና እና ችግር የሚፈጥር እንዲሁም ህገመንግስቱንና መሰረታዊ የህግ መርሆዎችን የሚጥስ ነው::

1) በአንቀጽ 74/1/ሠ መሰረት ኤጀንሲው የውጭ ማህበራትን የማይመዘግብ ስለሆነ አገር በቀል ማህበራት ህጋዊ ሰውነት ማገኘት ወይም በኤጀንሲው መመዝገብ እንዳይችሉ ያደርጋቸዋል::
2) አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከ10 በመቶ በላይ ገቢያቸውን ከውጭ በማግኘታቸው ምክንያት ብቻ እንደ ውጭ ድርጅቶች እንዲቆጠሩ ያደርጋል:: ስለሆነም ይህ አንቀጽ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያ ህግ መሰረት የተቋቋሙ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ያላቸውን ኢትዮጵያዊ ዜግነት የማግኘት መብት ይጥሳል:: ይህ ደግሞ በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው አካላት ዜግነት የሚያገኙት በተቋቋሙበት ሀገር ነው የሚለወን መሠረታዊ የህግ መርህ የሚጻረር ነው:: በዚህ ረገድም በኢትዮጵያ ንግድ ህግ ላይ እንደተመለከተው ገቢውን ከየትም ቢያገኝ በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ተቋቁሞ በኢትዮጵያ ባለስልጣን በመመዝገቡ ምክንያት ብቻ አንድ ኩባንያ የኢትዮጵያዊ ዜግነት ይኖረዋል ከሚለው ጋር ይጋጫል::
3) ይህ አንቀጽ ከአንቀጽ 16/6 ጋር አብሮ ሲታይ አብዛኞቹ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሰብዓዊ መብቶች፣ ግጭቶችን በመፍታት፣ በዜግነትና በማህበረሰብ ልማት፣ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ እና የፍትህ ስርዓትን በማሻሻል ስራዎች ላይ እንዳይሳተፉ ያግዳል:: ይህ በህገመንግስቱ አንቀጽ 31 ላይ የተቀመጠውን የዜጎችን ለማንኛውም ህጋዊ አላማ

የመደራጀት መብት የሚጥስ ነው። እንዲሁም ይህ አንቀጽ በኢትዮጵያ ውስጥ የጠንካራ ሲቪል ማህበረሰብ እድገትን የሚያቀጭጭ እና በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ሂደት ውስጥ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ሊኖራቸው የሚገባውን ሚና በጣም ዝቅ የሚያደርግ ነው።

4) ይህ አንቀጽ ከአንቀጽ 118/2 ጋር አብሮ ሲታይ አብዛኞቹ አገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚንስትሩ/በኤጀንሲው ውሳኔዎች ላይ ለፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት ያሳጣቸዋል።

5) በዚህ አንቀጽ ሀብት የሚለው ቃል ምንን እንደሚያመለክት በግልጽ አልተቀመጠም። ስለሆነም ቃሉ የድርጅቱን በጀት ለማመልከት ነው ወይስ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሀብቶቹን የሚመለከት ነው የሚል ጥያቄ ያስነሳል። ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሀብቶችን የሚመለከት ነው ቢባል እንኳዋ ገና ህጋዊ ሰውነት ያላገኘ እና በመመስረት ላይ ያለ ድርጅት በዚህ መልክ ሊፈረጅ የሚችል ሀብት እንዴት ይኖረዋል? በህግም ቢሆን አንድ ድርጅት ሀብት እንዲኖረው በቅድሚያ ህጋዊ ሰውነት ሊኖረው ይገባል።

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች የሀብት ምንጭ ከሀገር በቀል ድርጅቶች ዜግነት ጋር ፈጽሞ ሊያያዝ አይገባም።

> *የማሻሻያ ሀሳብ፡- ከዚህ ገደብ ጀርባ ያለው ግምት በአገሪቱ የሚገኙ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት በውጭ ለጋሾች ላይ ጥገኛ መሆናቸው ለአገራዊና ሕዝባዊ ጥቅሞች ተቃራኒ ለሆነ ተፅዕኖ ያጋልጣቸዋል የሚል ስጋት ከሆነ መርሃ ግብሮቻቸው ህጋዊና ህጋዊ ተቀባይነት ያለውን የህዝቡን ፍላጎት የሚያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ የተሻለ ውጤት ማግኘት ይቻላል። ይህም በሚቋቋሙበት ጊዜ እና በየጊዜው የሚያቀርቧቸውን ሪፖርቶች በመገምገም በቀላሉ ሊፈጸም ይችላል። የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትና ማህበራት አገራዊ ባህሪ በዋነኝነት የሚገለጸው በአባላት ማንነት እንደመሆኑ የገቢ ምንጫቸው ህጋዊ እስከሆነ ድረስ ከውጭ በመሆኑ ብቻ የተለየ ገደብ ሊጣልባቸው አይገባም። በተጨማሪም ድርጅቶችን ከለጋሾች ርዳታ ጥገኝነት ለማላቀቅ ረዥም ጊዜ የሚወስድ እና በአብዛኛውም በድጋፍ እና የማበረታቻ እርምጃዎች የሚከናወን እንጂ ዜጎች ካሉበት የድህነት ደረጃ እና ለበጎ አድራጎት ስራ መዋጮ የማድረግ ባህላችን ኋላ ቀር መሆኑ ሲታይ የውጪ ጥገኝነትን በህግ አስገዳጅነት ማስቀረት የማይቻል ነው ። ይልቁንም ይህ አይነቱ ድንጋጌ ብዙዎቹ ሀገር በቀል ድርጅቶች ስራቸውን እንዲያቆሙ እና ተጠቃሚዎቻቸው እንዲበተኑ ስለሚያደርግ ማህበራዊ ቀውስ ሊፈጥር የሚችል መሆኑ ታሳቢ ቢደረግ መልካም ነው። ስለዚህ ይህ አንቀጽ ማንኛውም በኢትዮጵያ ውስጥ የተመዘገበ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋም ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላው መሆኑን በሚገልጽ ሁኔታ መስተካከል አለበት።*

**3. የተፈጻሚነት ወሰን (አንቀጽ 3)**

በሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በያንዳንዱ ክልል ከሚተዳደሩ ይልቅ በፌደራል መንግስቱ ህግ እንዲሸፈኑ መደረጉ የዚህ አንቀጽ አዎንታዊ ገጽታ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው። ነገር ግን ይህ አንቀጽ እንደ ብሔራዊ ተቋም

ለመቆጣር ድርጅቶች ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች መስራት አለባቸው የሚል እንደምታ ያለው ይመስላል:: ይህ ደግሞ አዲስ ለሚቋቋሙ ድርጅቶች ለመተግበር የሚያስቸግር ይሆናል:: ለቁጥጥር አሰራርም ቢሆን የአዋጁ ተፈፃሚነት ድርጅቶችና ማህበራት የሚሰሯቸውን እና ሊሰሩ ያቀዷቸውን ተግባራት ከግምት ውስጥ አለማስገባቱ ችግር ሊፈጥር ይችላል::

**የማሻሻያ ሀሳብ:-** የድርጅቶቹ ብሔራዊ ባህሪ በመቋቋሚያ ሰነዳቸው ከአንድ በላይ በሆኑ ክልሎች ለመስራት ባላቸው እቅድ ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ቢሆን የተሻለ ይሆናል:: ብሔራዊ ባህሪ ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚሰሩ ድርጅቶችና ማህበራትም በዚህ አንቀጽ ቢሸፈኑ አግባብነት ያለው ይሆናል:: አዋጁ ተፈፃሚ የማይሆንባቸው ማህበራት ለምሳሌ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሕብረት ስራ ማህበራት፣ የአባላትን የፋይናንስ ጥቅም ለመጠበቅ የሚቋቋሙ ማህበራት፣ ወዘተ... በዝርዝር ቢገለፁም መልካም ነው:: በተጨማሪም ለበአድ እና ለማህበራት እንደተደረገው ሁሉ በውጭ ሀገር የተቋቋሙ ማህበራትን ምዝገባ፣ ፈቃድ አሰጣጥ እና አሰራር የሚመለከቱ ዝርዝር ድንጋጌዎች በአዋጁ በአንድ ክፍል ተለይተው ቢገኙ አዋጁ የተሻለ ግልጽ እና ለአፈጻጸም የቀለለ ይሆናል::

## ክፍል ሁለት:- ስለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ መቋቋም

### 5. የኤጀንሲው አላማዎች (አንቀጽ 5)

በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ዓላማዎች በመግቢያው ፓራግራፍ 2 እና 4 ላይ የአዋጁን አስፈላጊነት በተመለከተ የተቀመጠውን አያንጸባርቁም:: ይልቁንም የመቆጣጠር ገፅታው በተለይ ጎልቶ የወጣ ይመስላል::

**የማሻሻያ ሀሳብ:-** ከተዘረዘሩት ዓላማዎች በተጨማሪ ኤጀንሲው የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትና ማህበራት እራሳቸውን በራሳቸው እንዲቆጣጠሩ፣ አቅማቸውን በተሟላ መልኩ እንዲጠቀሙና የተቋቋሙበትን ህጋዊ ዓላማ ለማሳካት እንዲችሉ ለመደገፍና አቅማቸውን ለማጎልበት ኃላፊነት እንዳለበት የሚጠቁሙ ንዑስ አንቀጾች ቢጨመሩበት የአዋጁን ዓላማዎች በተሻለ መልኩ ሊያንጸባርቅ ይችላል::

### 6. የኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት (አንቀጽ 6)

በዚህ አንቀጽ ከተቀመጡት የኤጀንሲው ሥልጣን እና ተግባራት ውስጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን የላቀ አስተዳደርን ከማበረታታትና ሁኔታዎችን ከማመቻቸት አኳያ ኃላፊነት የተሰጠው መሆኑ መልካም ገጽታ ሆኖ ይታያል:: ሆኖም ግን የአንቀጹ ድንጋጌዎች በዋናነት የሚያንጸባርቁት የኤጀንሲውን የቁጥጥር ሥልጣን እና ተግባራት ነው:: እንዲሁም በኤጀንሲው ሥልጣንና ተግባራት ዝርዝር ውስጥ በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትና ማህበራት አቅም ግንባታና ድጋፍ አኳያ የሚኖረው ሚና አይንጸባረቅም::

**የማሻሻያ ሀሳብ:-** ከላይ ለአንቀጽ 5 የተመለከተው ለዚህም አንቀጽ ከግምት ውስጥ ቢገባ::

**7. የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምክር ቤት (አንቀጽ 13)**

አዋጁ በዚህ አንቀጽ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች እና ሌሎች በሚኒስትሩ የሚመደቡ የመንግስት አካላትን በአባልነት ያቀፈ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምክር ቤት ያቋቁማል፡፡ በንዑስ አንቀጽ ሦስት ላይም ሚኒስትሩ ኅብረተሰቡን የሚወክሉ ሁለት አባላትን ሊመድብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ ነገር ግን በጉዳዩ ዋነኛ ባለድርሻ የሆኑት የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትና ማህበራት በምክር ቤቱ ውስጥ አልተወከሉም፡፡ ለምክር ቤቱም ምንም ዓይነት የአሰራር ሥነ ሥርዓት ያልተቀመጠለት በመሆኑ የባለጉዳዮቹን ድርጅቶችና ማህበራት ሃሳብ እንኳ መጠየቅ አይጠበቅበትም፡፡ ስለሆነም ምክር ቤቱ በአንቀጽ 14 መሰረት ሊያራምደው የሚጥረው መልካም አስተዳደር ዋነኛ መርሆዎች የሆኑትን ተሳትፎንና ግልጽ አሰራርን ዋጋ የሰጠ አይመስልም፡፡ ኅብረተሰቡን የሚወክሉ የተባሉት አባላትም የሚመረጡት ባለድርሻ በሆኑት ማህበራት እና በአድ ሳይሆን መካተትም ሆነ አመራረጥ ሙሉ በሙሉ በኤጀንሲው እና በሚኒስትሩ ብቻ ነው፡፡ በአጠቃላይ የምክር ቤቱ አባላት በዋነኝነት በመንግስት አካላት በመወሰኑ እንዲሁም የማማከር ሥነ ሥርዓት ያልተበጀለት በመሆኑ በሙሉ አቅሙ ሊያበረክት የሚችለውን ያህል አስተዋጽኦ ማበርከት የሚችል አይመስልም፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ምክር ቤቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን በማስተዳደር ዙሪያ ከተሰጠው ከፍተኛ ሥልጣንና ኃላፊነት አኳያ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትና ማህበራትን ሃሳብ ሊያቀርቡ የሚችሉ በቂ ቁጥር ያላቸው ተወካዮች ድምጽ የመስጠት መብት ኖሯቸው በአባልነት ቢካተቱ አግባብነት ያለው ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሚኒስትሩ ኅብረተሰቡን የሚወክሉ አባላትን የሚመርጥበት መመዘኛ በአዋጁ ቢቀመጥ ይመረጣል፡፡

**8. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር (አንቀጽ 14)**

የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ምክርቤት ሥልጣንና ኃላፊነት ኤጀንሲውን እና ሚኒስትሩን የቁጥጥር ተግባራቸውን በተመለከተ ለማገዝ የተቋቋመ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ምክር ቤቱ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አስተዳደር የበላይ አካል መሆኑ በንዑስ አንቀጽ 1/ሠ ላይ የተገለፀ ቢሆንም ተጠሪነቱ ለሚኒስትሩ ይመስላል፡፡ በሌላ በኩል ምክር ቤቱ ከማማከርና ከማገዝ ያለፈ ግልጽ ስልጣን የተሰጠው አይመስልም፡፡ በተለይም በኤጀንሲው ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመቀበልና የማስተናገድ ሥልጣን የለውም፡፡ እንዲሁም በምክር ቤቱና በኤጀንሲው መካከል ያለው የተጠያቂነት ግንኙነት በግልጽ አልተቀመጠም፡፡ ለምሳሌ የኤጀንሲው ኃላፊዎች ቢያጠፉ ጉዳዩን መርምሮ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አልተሰጠውም፡፡ በውሳኔ አሰጣጥም ባለጉዳዮችን ማሳተፍም ሆነ ሃሳብ መቀበል አልተጠቀሰም፡፡ በዚህ ሁኔታ ትርጉም ባለው መልኩ የበላይ አካል ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡

ለምክር ቤቱ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዘንድ የመልካም አስተዳደር መርህ እንዲኖር ጥረት የማድረግ ኃላፊነት መስጠቱ አግባብ ቢሆንም ይህን ኃላፊነት ምክር ቤቱ እንዴት ተግባራዊ እንደሚያደርገው አልተብራራም፡፡

***የማሻሻያ ሀሳብ፡-*** *የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አስተዳደር የበላይ አካል እንደመሆኑ ምክር ቤቱ በኤጀንሲው እና በሚኒስቴሩ የተሰጡ ውሳኔዎችን የመከለስ፣ የመልካም አስተዳደር መለኪያዎችን የማውጣት እና በአጠቃላይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አስተዳደርን በበላይነት የመቆጣጠር ሥልጣን ሊሰጠው ይገባል፡፡ እንዲሁም ምክር ቤቱ በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ዘንድ የመልካም አስተዳደር መርህ እንዲኖር ጥረት የማድረግ ኃላፊነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው የራስ ቁጥጥርን በማበረታታትና ለውስጥ የቁጥጥርና የአስተዳደር ስርዓት ዝቅተኛ መመዘኛዎችን በማውጣት መሆን እንዳለበት መጠቀስ አለበት፡፡*

**ክፍል ሶስት፡- የበጎ አድራጎት ድርጅቶች**

***9. የበጎ አድራጎት ድርጅት ትርጓሜ (አንቀጽ 16)***

*በዚህ አንቀጽ የበጎ አድራጎት ድርጅት ከማህበራት ተለይቶ ትርጉም መሰጠቱ አሁን በስራ ላይ ካለው ህግ በተሻለ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን ባህሪና አደረጃጀት ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ በአንቀጽ 16/3 ለበጎ አድራጎት ዓላማ የተሰጠው ትርጉምም አግባብነት ያለው ሆኖ ይታያል፡፡ አንቀጽ 16/3 ሰብዓዊ መብቶች፣ ሰላም፣ ዴሞክራሲ እና ማህበራዊ ፍትህን ጨምሮ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሰፊ የመንቀሳቀሻ መስክ ይሰጣል፡፡ ይሁንና በተለያዩ ዘርፎች የሚደረግ ምርምርና ጥናት ለሀገር ልማትና ዕድገት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሚና ቢኖረውም ራሱን እንደቻለ ዓላማ ተደርጎ በአንቀጽ 16/3 ከተዘረዘሩት ዓላማዎች ውስጥ ስልተካተተ በምርምር መስክ ላይ አተኩረው ለሚንቀሳቀሱ ማህበራትና ድርጅቶች በር እንዲከፍት ተደርጎ ቢካተት ይጠቅማል፡፡ እንዲሁም መንግስት በአሁኑ ወቅት ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ከሚሰጠወ ትኩረት አንጻር በጎ አድራጎት ድርጅቶች የአርብቶ አደሩን ህይወት ለመለወጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራት በዚህ አንቀጽ ከተዘረዘሩት አላማዎች ውስጥ ቢካተቱ የተሻለ ነው፡፡*

*በአንቀጽ 16/6 በውጭ አገር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የተጣለው ገደብ የቀደሙትን አንቀጾች ይቃረናል፤ በአሁኑ ጊዜ በተጠቀሱት መስኮች ተሰማርተው የሚገኙ ብዙ ዓለም አቀፍ ተቋማት ላይም አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ ከአገር እና ከአገር በቀል የሲቪል ማህበረሰብም ጥቅም አኳያ የውጭ ድርጅቶች አዳዲስ ሃሳቦችን እና አሰራሮችን በማስገባትና በቀጥታም ቢሆን እያደረጉ ያሉትንና ሊያደርጉ የሚችሉትን አስተዋጽኦ ያገናዘበ አይመስልም፡፡ በዚህ ረቂቅ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች የተነሳ ብዙዎቹ አገር በቀል ድርጅቶች የውጭ ባህሪ የሚሰጣቸው ከሆነ አብዛኛውን የሲቪል ማህበረሰብ ከነዚህ መስኮች የማስወጣት ውጤት ሊኖረውም ይችላል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ገደብ ሊጠበቅ የታሰበው ህጋዊ ጥቅም ምን እንደሆነም ግልፅ አይደለም፡፡*

***የማሻሻያ ሀሳብ፡-*** *በአንቀጽ 16/6 በውጭ አገር የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ላይ የተጣለው ገደብ ህገ መንግስቱን የሚቃረን መሆኑና ከምክንያቱ ጀምሮ አፈፃፀሙ የሚኖረው ውጤት ከግምት ውስጥ ገብቶ ገደቡ ሊነሳ ይገባል፡፡*

**10. የበጎ አድራጎት ድርጅት አይነቶች (አንቀጽ 17)**

እንደሚታወቀው በኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ዕድገት ማነቆ ከነበሩት ችግሮች መካከል አንዱ የድርጅቶች ህብረት በህግ እውቅና ያልተሰጠው መሆኑ ነበር። ከዚህ አኳያ አንቀጽ 17/3 ለድርጅቶች ህብረት እውቅና መስጠቱ እጅግ የሚደገፍ ነው። በሌላ በኩል አንቀጹ የድርጅቶች ህብረት ቀጣይነት ያለውና መደበኛ ተቋም ሆኖ በመቋቋም ህጋዊ ሰውነት ሊኖረው የሚችል መሆኑ ወይም አለመሆኑ አልተገለጸም። የህብረቱ ዓላማም የአባላቱን ሥራ በማስተባበር ላይ ብቻ የተወሰነ ይመስላል።

> *የማሻሻያ ሀሳብ፡- የድርጅቶች ህብረት ማቋቋም መሰረቱ የመደራጀት መብት እንደመሆኑና በረቂቅ አዋጁ ያልተመዘገቡ ማህበራት የተከለከሉ ከመሆኑ አንጻር ተመዝግቦ በመደበኛ ተቋምነት መንቀሳቀስ የሚያስችል አንቀጽ ቢካተት የተሻለ ይሆናል። ዓላማዎቹን በተመለከተም የአባላቱን ሥራ ከማስተባበር ባሻገር ለተወሰነ ህዝባዊ ጥቅም በጋራ መስራት፣ የሲቪል ማህበረሰቡን ጥቅሞች ማስከበር እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ቢያካትት የበለጠ ጥቅም ይኖረዋል። አንቀጹ ከአንቀጽ 60 ጋር ያለው ዝምድናና ልዩነትም ቢመለከት በጎ ነው።*

**11. የበጎ አድራጎት ማህበራት /አንቀጽ 50/**

በኢትዮጵያ የሚገኙት አብዛኞዎቹ ሀገር በቀል ማህበራትና ድርጅቶች በረቂቅ ህጉ ደንጋጌዎች መሠረት በበጎ አድራጎት ማህበርነት የሚፈረጁ ሆነው ሳለ በረቂቁ በጎ አድራጎት ማህበራትን በሚመለከት ያለው አንድ አንቀጽ /አንቀጽ 50/ ብቻ ነው። በተጨማሪም አንቀጽ 50/2/ ማህበራት እና በአድን የሚመለከቱት ደንጋጌዎች በበጎ አድራጎት ማህበራት ላይ ይፈጸማሉ ስለሚል በአንድ ጉዳይ ላይ ለማህበራትና ለበአድ የተለያዩ ድንጋጌዎች ሲኖሩ /ለምሳሌ ከገቢ ግብር ነጻ ስለመሆን/ በበጎ አድራጎት ማህበራት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑት የትኞቹ ድንጋጌዎች እንደሆኑ ግልጽ አይደለም። በአንጻሩ ረቂቅ አዋጁ በኢትዮጵያ በብዛት ለማይገኙት የበጎ አድራጎት ተቋም፣ የዘለቄታ በአድ እና የአደራ በአድን ለመሳሰሉ ድርጅቶች ዝርዝር ድንጋጌዎች አካትቶ ይታያል። ስለሆነም በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የሚመለከተው ክፍል በዋናነት በበጐ አድራጎት ማህበራት ላይ በማተኮር ዝርዝር ድንጋጌዎች እንዲኖሩት ቢደረግ የተሻለ ይሆናል።

**ክፍል አራት፡- ማህበራት**

**11. የማህበራት ትርጉም (አንቀጽ 60)**

በዚህ አንቀጽ ለማህበር ሰፋ ያለና የተለያየ ባህሪ ያላቸውን ስብስቦች የሚያካትት ትርጉም ተሰጥቶታል። ማህበር ለማቋቋም የሚያስፈልገው የመስራች አባላት ቁጥር አስር መሆኑና ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ በአምስት አባላት የተቋቋመ ማህበር ሊመዘገብ የሚችል መሆኑ ተደንግጓል። በአንቀጽ 17 ለድርጅቶች እንደተደረገው ሁሉ ማህበራትም ህብረት ለማቋቋም የሚችሉ መሆኑ ተገልጿል። በዚህ አንቀጽ የማህበራት ዓላማ ውሱን አለመደረጉ፣ ህብረት ማቋቋም መቻሉ

እና በማህበራት መካከል ያለውን የባህሪ ልዩነት አካትቶ የያዘ መሆኑ እንደ ጠንካራ ጎን ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል በሁለቱም ንዑስ አንቀጾች የመስራች አባላት ቁጥር መወሰኑ ከአስር በታች ቁጥር ያላቸው ዜጎችን የመደራጀት መብት ይገድባል፡፡ ይህ ደግሞ የህገመንግስታዊነት ጥያቄ የሚያስነሳና ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን አለም አቀፍ ስምምነቶችም የሚቃረን ነው፡፡ አሁን በስራ ላይ ካለውና ከአርባ ስምንት አመታት በፊት ከወጣውና ሁለት እና ከዚያ በላይ ሰዎች ማህበር ማቋቋም እንደሚችሉ ከሚደነግገው የፍትሃ ብሔር ህግ (አንቀጽ 404) አንጻር እንኳን ሲታይ ወደኋላ እንደመመለስ ይቆጠራል፡፡ በአጠቃላይ ማህበር ለመመስረት የሚያስፈልገውን አነስተኛ የመስራች አባላት ቁጥር መወሰን ያለምንም የፖሊሲ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ከአስር በታች አባላት ያሏቸውን የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡ በአንቀጽ 2/3 አተረጓጎም ብዙ ኢትዮጵያውያን እንደ ውጭ ማህበር ለመመዝገብ ሊገደዱ የሚችሉ እንደመሆኑ በአንቀጽ 60/2 ላይ የውጭ ማህበራት መገለላቸውም ተመሣሣይ የህገመንግስታዊነት ጥያቄ ያስነሳል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ረቂቅ አዋጁ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቁጥር ያላቸው ሰዎች ማህበር ለመመስረት እንደሚችሉ ቢደነግግ የህገመንግስቱን አንቀጾች በተሻለና አግባብነት ባለው መልኩ መተግበር ያስችላል፡፡ የመደራጀት መብት የተለየ የህዝብ ጥቅም ሲኖር ብቻ በችሮታ የሚሰጥ ሳይሆን መሠረታዊ መብት መሆኑንም በበለጠ ያሳያል፡፡ አንቀጽ 60/4ን በተመለከተ ከላይ በአንቀጽ 17 አኳያ የሰጠነው አስተያየትን ይመለከቷል፡፡

**12. የማህበራት መብቶችና ግዴታዎች (አንቀጽ 62)**

አንቀጽ 62/1 ማንኛውም ማህበር ለአዲስ አባላት ክፍት መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይህም ረቂቅ አዋጁ ሰፊ የአባላት መሰረት ያደረገ የማህበር ዓይነትን ብቻ እውቅና የሚሰጥ ያደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ መስራች አባላት በመተዳደሪያ ደንባቸው የአባላቸውን ቁጥር ለመወሰን ወይም አዳዲስ አባላት ላለመቀበል ያላቸውን መብት የሚቃረን ሆኖ ይታያል፡፡ በመርህ ደረጃ አዲስ አባላትን የመቀበል ወይም ያለመቀበል ውሳኔ የአባላቱ/የጠቅላላ ጉባዔው ሊሆን ሲገባ በረቂቁ ይልቁንም አዲስ አባላትን ለመቀበል ማህበራቸውን ክፍት እንዲያደርጉ ይገደዳሉ፡፡

በአንቀጽ 62/6 ደግሞ የፌደራል ስያሜ ወይም ባህሪ ያላቸው ማህበራት የስራ ቦታና የአባላት ጥንቅር ቢያንስ የአምስት ክልሎች ውክልና ያለው መሆን አለበት፡፡ ይህ ግዴታ በሚከተሉት ሦስት ምክንያቶች አግባብነት የለውም፡፡

- አንደኛ፡- አንድ ብሔራዊ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋም በክልሎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የመክፈት ዕቅድ ቢኖረውም በሚቋቋምበት ግዜ በአዲስ አበባ ወይም በአንድ የክልል ከተማ ብቻ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡ ገና ከመቋቋሙ ሕጋዊ እውቅና እንኳን ሳያገኝ በአምስት ክልሎች ጽ/ቤት እንዲከፍት ማስገደድ ምክንያታዊ አይሆንም፡፡
- ሁለተኛ፡- የአንዳንድ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የስራ ባህሪ ብሔራዊ ቢሆንም በክልሎች ጽ/ቤት መክፈት አያስፈልገውም፡፡ ለምሳሌ በብሔራዊ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ

ጥናትና ውይይት ለማካሔድ ያቀደ ማህበር የፌደራል ፖሊሲ አውጭዎችን በሙሉ በአዲስ አበባ ስለሚያገኛቸው በዚያ ብቻ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡ አልፎ አልፎ በክልሎች መረጃ የመሰብሰብና የውይይት መድረኮችን የማዘጋጀት ስራ ቢሰራም ጽ/ቤት መክፈት አያስፈልገውም፡፡

ሦስተኛ፡- የአንድ ማህበር ፌደራል ስያሜ ማህበሩ ለወደፊት ያለውን በብሔራዊ ደረጃ የመንቀሳቀስ ራዕይ የሚያመላክት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሥራው ቦታና የአባላት ጥንቅር አምስት ክልሎችን እንዲወክል ከመጀመሪያው ማስገደድ የማህበሩን ራዕይ መገደብና ክልላዊ ውሱንነትን ማበረታታት ይሆናል፡፡

ፌደራላዊ ባህሪ በአምስት ክልሎች ጽ/ቤት መክፈትን የግድ አይልም፤ የአባላት ምልመላ መለኪያዎችም መወሰን ያለባቸው በማህበሩ አባላት ብቻ ነው፡፡ በአጠቃላይ ፌደራል ባህሪና ስያሜ ባላቸው ማህበራት ላይ የተጣለው ግዴታ በቂ ምክንያት የሌለውና ወጪ አበራካች ከመሆኑ በተጨማሪ በማህበራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የሚገባ ነው፡፡

የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 7 የኢትዮጵያውያን ብዙሃን ማህበራት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና በምርጫ ሂደት በንቃት መሳተፍ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡ ይህ ድንጋጌ በሌሎች ማህበራት ላይ የሚኖረው እንደምታ ግልፅ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ ሌሎች ማህበራት በነዚህ መስኮች መሳተፍ አይችሉም የሚል ግልፅ ድንጋጌ ባይሆንም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና በምርጫ ሂደት በንቃት መሳተፍ ለብዙሃን ማህበራት ብቻ የታጠረ ያስመስለዋል፡፡ በረቂቅ ህጉ ላይ ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር በተደረገው ውይይት የተገለጸውም ከምርጫና ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጋር የተያያዙ ስራዎች ለብዙሀን ማህበራት ብቻ የተፈቀዱ ናቸው የሚል እንድምታ ያለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሕገመንግሰቱ ዕውቅና የተሰጣቸውን የዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች መገደብ ከመሆንም አልፎ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 60/1/ ማህበራት ለማንኛውም ህጋዊ አላማ ሊቋቋሙ እንደሚችሉ ከተቀመጠው ድንጋጌ ጋር ይቃረናል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የማህበራት የአደረጃጀት ቅርፅ እና አዲስ አባላት መቀበል ወይም አለመቀበል ለመስራች አባላት መተው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ፌደራላዊ ዕውቅናን በተመለከተ ከማህበራቱ ስያሜና የአባላት ጥንቅር ይልቅ በመቋቋሚያ ሰነዳቸው ያስቀመጡትን ዓላማና ራዕይ መሰረት ያደረገ ቢሆን የተሻለ ይሆናል፡፡ ከዚህም አኳያ ህጉ በተለያዩ ክልሎች የሚንቀሳቀሱ ማህበራት ብሔራዊ ጥምረት እንዲፈጥሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ቢያተኩር የተሻለ ውጤታማ ሊሆን ይችላል፡፡ አንቀጽ 62/7 ሌሎች ማህበራትም በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እና በምርጫ ሂደት መሳተፍ እንደሚችሉ ቢያስቀምጥ የበለጠ ግልፅና ከሕገመንግስቱ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡

**13. የማህበራት አደረጃጀት (አንቀጽ 63)**

አንቀጽ 63/2 አንድ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ፣ የስራ አስፈፃሚ እና ኦዲተር እንደሚኖረው ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ የማህበራትን አደረጃጀት መወሰኑ አባላት የማህበራቸውን ቅርፅ ለመወሰን ያላቸውን

ነጻነት የሚገድብ መስሎ ይታያል:: በሌላ በኩል ግን የስራ አስፈፃሚውን ሥልጣንና ኃላፊነት አለመወሰኑ ለአባላት የተሻለ ነፃነት የሚሰጥ መሆኑ እንደ ጠንካራ ጎን የሚታይ ነው::

ይህ የማህበራቱ ነጻነት እንዳለ ሆኖ የማህበራትን የውስጥ ቁጥጥርና ተጠያቂነት ከማጠናከር አንጻር ረቂቅ ህጉ በተለመደው አሰራር የሚኖረውን የማህበራትን አወቃቀር በተከተለ መልኩ /ለምሳሌ ጠቅላላ ጉባኤ፣ የመጨረሻው ውሳኔ ሰጪ አካል ሆኖ ነገር ግን ፖሊሲ ለማውጣት እና ማኔጅመንቱን የሚቆጣጠር የስራ አመራር ቦርድ የሚኖርበት /General Assembly - Board- Management/Executive/ አሰራር እንዲሁም የድርጅቱ ከፍተኛ አካል ቦርድ የሚሆንበት /Board Led/ ጊዜ/ የያንዳንዱ የማህበሩ አካል ስልጣንና ተግባር ምን ሊሆን እንደሚገባ መመዘኛዎችን ቢያስቀምጥ እንዲሁም የግልጽነት እና ተጠያቂነት መርሆዎችን በማስፈን ረገድ መዋቅሩ እና አካላቱ ሊከተሏቸው የሚገቡ ግዴታዎችን በግልጽ ቢያካትት የተሻለ ነው:: ስለሆነም ለምሳሌ ረቂቅ ህጉ «ማህበሩ በቦርድ የሚመራ ሲሆን የሚከተሉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ» በማለት ዝርዝር ድንጋጌዎችን ሊያካትት ይችላል:: በተመሳሳይ መልኩ የሙያ እና የሕዝብ ማህበራት የሚኖሯቸውን አካላት /ለምሳሌ ጠቅላላ ጉባዔ/ምክር ቤት፣ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፣ እንዲሁም ስራ አስኪያጅ/ ስልጣንና ተግባር እንዲሁም እና ተጠያቂነትና ቁጥጥርን በተመለከተ ሊከተሉ የሚገባቸውን አሠራር በሚመለከት መስፈርቶችን ቢያስቀምጥ ለውስጥ ቁጥጥር የተሻለ ይሆናል::

**14. የጠቅላላ ጉባዔው ስልጣንና ተግባራት (አንቀጽ 64)**

በንዑስ አንቀጽ 1/ሐ የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት የሚለወጥበትን ውሳኔ ለመስጠት አጠቃላይ ስብሰባ ማስፈለጉ ግልፅ አይደለም:: የዋና መስሪያ ቤት ለውጥ ሲባል ከአንድ ክፍለ ከተማ ወደሌላ ወይም ከአንድ ህንጻ ወደሌላ ማለት ከሆነ በስራ አስፈጻሚው ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ነው:: በተመሣሣይ መልኩ አጠቃላይ ስብሰባ በአመት ሁለት ወይም ሦስት ጊዜ ብቻ የሚጠራ ከመሆኑ አኳያ በንዑስ አንቀጽ 1/ሠ ላይ በማህበሩ የፖሊሲና ሰትራቴጂ ጉዳዮች ላይ እንዲወስን የተሰጠው ስልጣን ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻል አይመስልም:: ይሁን እንጂ ቢባል የማህበሩ አባላት ቁጥር ከፍተኛ ከሆነ ለነዚህ ጉዳዮች ስብሰባ መጥራት አይቻልም:: የሆነ ሆኖ ረቂቅ አዋጁ የአጠቃላይ ስብሰባውን ይዘትና አወቃቀር በግልጽ አያስቀምጥም::

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** በዚህ አንቀጽ ዋና መስሪያ ቤትን ስለመለወጥና የማህበሩን የፖሊሲና ሰትራቴጂ ጉዳዮች ስለመወሰን ለአጠቃላይ ስብሰባው የተሰጡ ሥልጣንና ተግባራት ለስራ አስፈጻሚ ቦርድ ቢሰጡ የተሻለ ይሆናል::

**15. ከጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔዎች መለየት (አንቀጽ 65)**

በአንቀጽ 65/2 ማንኛውም አባል የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ህግን ወይም መተዳደሪያ ደንቡን የሚጥስ ሆኖ ከታየው ለኤጀንሲው ማመልከት እንደሚችል ተቀምጧል:: የጉባዔው ቃለ-ጉባኤ ለኤጀንሲው የሚላክ ከመሆኑ አንጻር የዚህ አንቀጽ አስፈላጊነት ግልፅ አይደለም:: ይልቁንም በአባላት መካከል አለመግባባት በተፈጠረ ቁጥር ጉዳዩን ወደ ኤጀንሲው በማምጣት የኤጀንሲውንም ሆነ የማህበሩን የስራ ጊዜ ከማጣበብ ያለፈ ጥቅም ያለው አይመስልም::

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ይህ አንቀጽ አስፈላጊ ስላልሆነ ቢወጣ ይሻላል::

**16. የጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች (አንቀጽ 66)**

በአንቀጽ 66/2 በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጠቅላላ ጉባዔ ካልተጠራ በማህበሩ ውስጥ ያሉ ሌሎች አማራጮች ሳይሟጠጡ በሰላሳ ቀናት ውስጥ በአንድ አባል ጥያቄ ብቻ በኤጀንሲው ሊጠራ እንደሚችል መደንገጉ በማህበራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ከመግባት አኳያ አግባብነቱ ያጠያይቃል፡፡ ጉባዔውን በሊቀመንበሩ በኩል ወይም በራሱ እንዲጠራ ለኤጀንሲው የተሰጠው አማራጭም ሆነ የሊቀመንበሩ ማንነት ግልፅ አይደለም፡፡ በአንቀጽ 66/3 ኤጀንሲው ለጠቅላላ ጉባዔው ሊቀመንበር ማቅረቡም ጉባዔው በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት አዲስ ሊቀመንበር ሊመርጥ የሚችል ከመሆኑ አንጻር አግባብነት የለውም፡፡ ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በሶስተኛው ስብሰባ በሚገኙት አባላት ምልዓተ ጉባዔ እንደተሟላ የሚቆጠር መሆኑ የተለመደ የስብሰባ ሰርዓት ሆኖ እያለ ይህ አይነቱ ድንጋጌ በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ እንዳይካተት በአንቀጽ 66/5 መከልከሉ ምክንያታዊ አይመስልም፡፡ በተጨማሪም አንቀጽ 66/5 ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ኤጀንሲው እንዲወስን ስልጣን መስጠቱ አግባብ አይደለም፡፡

> ***የማሻሻያ ሀሳብ፡-*** *በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ጠቅላላ ጉባዔ ካልተጠራ የአባላት 1/3ኛ ጉባዔው እንዲጠራ ሊቀመንበሩን ሊጠይቅ እንደሚችልና ይህ ካልሆነ ብቻ ተመሳሳይ ማመልከቻ ለኤጀንሲው ሊቀርብ እንደሚችል ማስቀመጡ የተሻለ ይሆናል፡፡ ጉባዔው በኤጀንሲው ሊጠራ የሚችለውም ስራ አስፈፃሚው የአባላቱን ጥያቄ ለማሟላት ያልቻለበት በቂ ምክንያት የሌለ ከሆነ ብቻ ቢሆን ይመረጣል፡፡ በዚህ መልኩ ጠቅላላ ጉባዔ በኤጀንሲው በሚጠራበት ጊዜ ስብሰባውን ማን ይምራው የሚለው ለጠቅላላ ጉባዔው አባላት መተው ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ምልዓተ ጉባዔ የሚሟላበትን ሁኔታ በተመለከተ አንቀጽ 66/5 የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በመተዳደሪያ ደንቦቻቸው ላይ ዲሞክራሲያዊ ደንቦችን በመከተል መወሰን እንዳለባቸው ብቻ ቢያስቀምጥ በቂ ነው፡፡*

**17. የኦዲተር ስልጣንና ተግባራት (አንቀጽ 67)**

አንቀጽ 67/1 የሚመለከተው በጠቅላላ ጉባዔው ስለሚሾም የውጭ ኦዲተር ከሆነ ኦዲተሩ የማህበሩን ገንዘብና ንብረት አስተዳደር እንዲቆጣጠር ማድረጉ ተግባራዊነቱ አስቸጋሪ ነው የሚሆነው፡፡ ምክንያቱም የውጭ ኦዲት የሚደረገው በአመት አንዴ ስለሆነ፡፡ እንዲሁም ኦዲተሩ ከማህበሩ ውጭ የሚመጣ ከሆነ ሪፖርቱ እንዴት የውስጥ ኦዲት ሪፖርት ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል ግልጽ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ኦዲተሩ ከማህበሩ አባላት መካከል እንዲሆን ከሆነ የታሰበው፤ እያንዳንዱ ማህበር ኦዲት ለማድረግ የሚችል የሙያ ብቃት ያለው አባል እንዲኖረው ማስገደድ የመደራጀት ነጻነትን የሚጋፋ ሲሆን ሙያው ያለው አባል ቢኖር እንኳን አባሉ የማህበሩን ገንዘብና ንብረት በየጊዜው ኦዲት ለማድረግ ጊዜውን እንዲያውል መጠበቁ አግባብ አይደለም፡፡ ስለኦዲተሩ የውስጥ ወይም የውጭ መሆንን በተመለከተ ያለው ብዥታ ስለ የውጭ ኦዲተር በሚደነግገው አንቀጽ 67/2 የበለጠ ተጠናክሯል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥና የተፈጠረውን ብዥታ ለማስወገድ በአንቀጽ 67/1 ላይ የተመለከተው ኦዲተር የውጭ ኦዲተር (የማህበሩ አባል ወይም ሰራተኛ ያልሆነ) መሆኑ በግልጽ ይቀመጥ፡፡

**18. አባላትን የሚመለከቱ መረጃዎች (አንቀጽ 68)**

በዚህ አንቀጽ ስለአባላት ሊያዙ የሚገባቸው መረጃዎች በግልጽ አልተደነገጉም፤ ይልቁንም ይህ የሚወሰነው ወደፊት በኤጀንሲው በሚወጣ መመሪያ ነው፡፡ ይህም ማህበራት ማንኛውንም መረጃ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ያስመስለዋል፡፡ በተለይም በአማርኛው ቅጂ የተቀመጠው «ዝርዝር ጉዳዮች» የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል እንደመሆኑ የአባላትን የግል ነፃነት የሚቃረን ሊሆን ይችላል፡፡ የመስራች አባላት ዝርዝር እና የስራ መሪዎች ማንነት ለኤጀንሲው የሚገለፅ ከመሆኑም አንጻር ሲታይ ስለ አባላት ዝርዝር መረጃ መጠየቁ አስፈላጊነቱ ግልፅ አይደለም፡፡ ይልቁንም አባላት በማህበራት ስላላቸው ተሳትፎ በመንግስት ክትትል የሚደረግባቸው ስለሚያስመስል ማህበራት አባላትን ለመመልመል እንዲቸገሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** በምዝገባ ጊዜ ከሚቀርበው የመስራች አባላት ዝርዝር ውጭ የማህበሩ ኃላፊዎች ስምና አድራሻ ብቻ ቢጠየቅ በቂ ስለሚሆን አንቀፁ በዚህ መልኩ ቢሻሻል፡፡ የሚጠየቀውን ዝርዝር መረጃ በተመለከተም ውሳኔውን ለኤጀንሲው ከመተው ይልቅ በግልፅ ቢደነገግ ይመረጣል፡፡

**ክፍል አምስት፡- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አመሰራረት፣ ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ**

**19. አመሰራረት (አንቀጽ 69)**

በአንቀጽ 69/3 የአማርኛና እንግሊዝኛ ቅጂዎች መካከል መጣረስ ያለ ይመስላል፡፡ የእንግሊዝኛው ቅጂ «የግዜ ገደብ ቢያልፍም» የሚለውን ትርጉም አያንፀባርቅም፡፡ በተጨማሪም በአንቀጹ በቂ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ምን እንደሆነ አልተገለፀም፡፡ ይህም የኤጀንሲውን ስልጣን ያለአግባብ ያሰፋዋል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የእንግሊዘኛው ቅጂ አፃፃፍ ከአማርኛው ጋር በሚጣጣም መልኩ ቢስተካከል፤ በቂ ምክንያት የሚለውም ሃረግ ቢያንስ ገላጭ በሆኑ ምሳሌዎች ቢብራራ የተሻለ ነው፡፡

**20. የመመስረት ውጤት (አንቀጽ 70)**

በአንቀጽ 70/3 በመቋቋም ላይ ያሉ ድርጅቶች እና ማህበራት ሊያሰባስቡ የሚችሉት ከፍተኛው የገንዘብ መጠን በሃምሳ ሺህ ብር ተወስኗል፡፡ በመጀመሪያ ገና ማህበሩ ህጋዊ ሰውነት የሌለው ከመሆኑ አንፃር ስለድርጅቱ ወይም ማህበሩ መደንገጉ ግልፅ አይደለም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ይህ የገንዘብ ጣሪያ በሦስተኛ ወገኖች ቃል የሚገባ የገንዘብ መጠንን እና በአባላት የሚደረግ መዋጮን የሚመለከት መሆኑ ወይም አለመሆኑ አልተጠቀሰም፡፡ አሁን ባለው አሰራር በመቋቋም ላይ ያሉ ማህበራት

ለምዝገባ ሲያመለክቱ ከለጋሽ ድርጅቶች ባቀረቡት የመርሃ ግብር ሃሳብ መሰረት ቃል ተገብቶላቸው ሲሆን የገንዘብ ድጋፉ የሚደረግላቸው ግን ከተመዘገቡ በኋላ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ በመቋቋም ላይ ያለ ማህበር የመቶ ሺህ ብር ስጦታ ቃል ቢገባለት ክልከላው እንደተጣሰ ይቆጠራልን? ወይስ አንቀጹ በማህበሩ እጅ የገባ ገንዘብን ብቻ ነው የሚመለከተው? በሌላ በኩል ደግሞ ከመስራች አባላት አንዱ የግል መኖሪያ ቤቱን በስጦታ ቢያበረክት የንብረቱ ዋጋ ከተጠቀሰው ገንዘብ በላይ ሊሆን ይችላል፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች የዚህ አንቀጽ ተፈፃሚነት ግልፅ አይደለም፡፡ በዚህ አንቀጽ የተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያም ቢሆን በተለይ ፌደራል ባህሪ ወይም ስያሜ ያላቸው ማህበራት ቢያንስ በአምስት ክልሎች ጽ/ቤት ከፍተው መንቀሳቀስ የሚጠበቅባቸው ከመሆኑ አንፃር ሲታይ እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ለሌሎች ማህበራትም ቢሆን እንደተመዘገቡ ወዲያው ስራ ከመጀመር ይልቅ ገንዘብ ወደማሰባሰብ እንዲገቡ ያስገድዳቸዋል፡፡

አንቀጽ 70/4 ለማህበራቸው ከፍተኛ ገንዘብ ያሰባሰቡ መስራቾችን ገንዘብ በመሰብሰባቸው ብቻ የሚቀጣ ሆኖ ይታያል፡፡ ለህጋዊ ዓላማ ለተመሰረተ ማህበር ገንዘብ ያሰባሰቡ ትጉሃን ሊመሰገኑ እንጂ ሊቀጡ አይገባም፡፡ ዓላማው በምስረታ ሂደት የሚሰበሰበው ገንዘብ አለመባከኑን ወይም ለግል ጥቅም አለመዋሉን ለማረጋገጥ ከሆነ የገንዘብ ጣርያና ቅጣት ከማስቀመጥ ይልቅ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ ቢጣል የተሻለ ውጤታማነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በዚህ መልኩ የተንቀሳቀሱ መስራች አባላት በፍትሐ-ብሔር ህጉም ሆነ በተሻሻለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎች አለአግባብ መበልፀግን በሚመለከተው ክፍል ሊጠየቁ ይችላሉ፡፡

በአንቀጽ 70/5 ስር የማህበሩ መቋረጥ የሚኖረው ውጤት አልተገለጸም፡፡ የማህበር መቋረጥ ምን ማለት ነው? ውጤቱስ ምን ይሆናል? የሚለው ተዘርዝሮ ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ መስራቾች በራሳቸው ስም ለማህበሩ ጥቅም የገቧቸው ግዴታዎችና ወጪዎች ቢኖሩ ህጋዊ ውጤታቸው ምን እንደሚሆን እንዲሁም ለማህበሩ አላማ የተሰበሰበ ገንዘብ ቢኖር ለማን መሰጠት እንዳለበት በዝርዝር ቢካተት ጥሩ ነው፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ከመመዝገባቸው በፊት በሚያሰባስቡት የገንዘብ መጠን ላይ ጣሪያ ከማስቀመጥ ይልቅ ለቁጥጥር የሚያመችና ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አያያዝ እንዲኖራቸው ቢደነገግ የተሻለ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በዚህ ሂደት የተሰበሰበው ገንዘብ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ባይመዘገብ ምን እንደሚደረግ ቢገለፅ አንቀጹ በይበልጥ የተሟላ ይሆናል፡፡

**21. የዘርፍ አስተዳዳሪዎች (አንቀጽ 71 እና 72)**

እነዚህ አንቀጾች የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ከማህበራት ምስረታ አንስቶ ወደፊትም ስለሚኖራቸው ሥልጣን፣ ኃላፊነትና ሚና የሚመለከቱ እንደመሆናቸው በረቂቅ አዋጁ የመጀመሪያ ክፍል ቢካተቱ የተሻለ ይሆናል፡፡ ወደይዘታቸው ስንገባ በተለይ የመጀመሪያው አንቀጽ አፃፃፍ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት አሰራር አመቺ ሁኔታ ከመፍጠር ይልቅ በቁጥጥርና እርምጃ በመውሰድ ላይ ያተኮረ ይመስላል፡፡ በዘርፍ አስተዳዳሪዎችና በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት መካከል ትብብር ሊደረግባቸው የሚችሉ መስኮችም አልተጠቀሱም፡፡ ሌላው ደግሞ በአንቀጽ 71/3 ላይ «በማቋቋሚያ

ህጉ መሰረት» የሚለው እና «አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል» የሚለው አገላለጽ ለዘርፍ አስተዳዳሪዎች አላግባብ ሰፊ የሆነ እና ያልተገለጸ ሥልጣን የሚሰጥ ይመስላል:: በዚህ ረገድ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ቁጥጥር ሲያደርጉ ሊከተሉት የሚገባው ስርዓት ምን ሊሆን እንደሚገባ እና ለምን አይነት ጥፋቶች የትኛውን አይነት ተመጣጣኝ እርምጃ እንደሚወስዱ በግልጽ አልተቀመጠም:: በተጨማሪም በአንቀጹ ሥር የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች በይግባኝ እንደገና የሚታዩበት ስርዓት አለመካተቱም ችግሩን ከማባባስ በተጨማሪ የኤጀንሲውን ሥልጣን ያሳንሰዋል:: ለዘርፍ አስተዳዳሪዎች የተሰጠው ሰፊ ስልጣን ማህበራትና በአድ ለተለያዩ የመንግስት አካላት እና ለኤጀንሲው ተጠያቂ እንዲሆኑ /dual accountability/ በማድረግ ለአሰራር አስቸጋሪ የሆነ ሁኔታ ከመፍጠሩም በላይ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ክትትልና ቁጥጥር ስርዓትም የተንዛዛ ያደርገዋል:: ስለሆነም የዘርፍ አስተዳዳሪዎች በራሳቸው የቅጣት እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የቴክኒክም ሆነ የአሰራር ጉድለት በበአድና ማህበራት ላይ በሚያገኙበት ጊዜ መወሰድ ስለሚገባው ርምጃ የውሳኔ ሐሳብ ለኤጀንሲው የሚያቀርቡበት እና በኤጀንሲው ውሳኔ መሠረት እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ ቢመቻች የተሻለ ነው::

> የማሻሻያ ሀሳብ፡- የዘርፍ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንና ኃላፊነት ከዜጎች መሰረታዊ የመደራጀት መብት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ዘርዘር ያለ ገደብ ከማበጀት አኳያ የዚህ አንቀጽ ይዘት እንደገና ቢታይ፤ በአንቀጹ ስር የተሰጡ አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን ለኤጀንሲው ከማሳወቅ ይልቅ የዘርፍ አስተዳዳሪዎች የውሳኔ ሐሳብ አቅርበው በኤጀንሲው እርምጃ የሚወሰድበት ሁኔታ ቢመቻች እንዲሁም እንዲህ አይነት እርምጃዎች በአስተዳደራዊ ስርዓትም ሆነ በፍርድ ቤት እንደገና የሚታዩበት አግባብም ቢገለፅ መልካም ነው:: በዘርፍ አስተዳዳሪዎችና በሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት መካከል ትብብር ሊደረግባቸው የሚችሉ መስኮች በተለይም የቴክኒክ ድጋፍ፣ የማማከር አገልግሎት እና አቅም ግንባታ የመሳሰሉ መስኮች ቢካተቱ ከህጉ መንፈስ ጋር የተሻለ ይጣጣማል::

**22. ምዝገባ (አንቀጽ 73)**

በረቂቅ አዋጁ መግቢያ ላይ እንደተገለጸው የህጉ መውጣት ካስፈለገባቸው ዋነኛ አላማዎች ውስጥ አንዱ የዜጎችን መብት ተግባራዊ የሚሆንበት አመቺ የህግ ማዕቀፍ ማስቀመጥ ነው:: ለዚህም ለማህበራት ምዝገባ የሚያስፈልጉ ቅድመ-ሁኔታዎችን በግልፅ ማስቀመጥ የግድ ነው:: በዚሁ መሰረት አንቀጽ 73/2 የምዝገባ ማመልከቻ ምን ምን መያዝ እንዳለበት በዝርዝር ካስቀመጠ በኋላ በንኡስ ቁጥር «ረ» ላይ ኤጀንሲው «ተመሳሳይ ሰነዶችንና ፎርሞችን» ሊጠይቅ እንደሚችል ይገልፃል:: የዚህ ንኡስ አንቀጽ አስፈላጊነቱ ግልፅ ካለመሆኑም በተጨማሪ ለኤጀንሲው አግባብ ያልሆነ ሥልጣን የሚሰጥ ይመስላል:: ኤጀንሲው እንደፈቀደው ተጨማሪ ሰነዶችን የሚጠይቅ ቢሆን የምዝገባው ሂደት የአዋጁን ዓላማ በሚፃረር መልኩ ረጅምና ውስብስብ የመሆን አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል::

በተጨማሪም ኤጀንሲው አስፈላጊው የምዝገባ ማመልከቻ ተሟልቶ በቀረበለት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መመዝገብ እንደሚገባው የጊዜ ገደብ ካለመቀመጡም በላይ ምዝገባ በሚከለክልበት ጊዜ የከለከለበትን ምክንያት በግልጽ ማስታወቅ እንዳለበት አልተደነገገም:: ለቀረበለት የምዝገባ ማመልከቻ

መልስ ባይሰጥ ውጤቱ ምን እንደሚሆንም አልተገለጸም፡፡ ይህ ደግሞ ኤጀንሲው በዚህ ረገድ ስራውን ማከናወኑንና የዜጎች የመደራጀት መብትም መጠበቁን ለመከታተል አስፈላጊ ይመስለናል፡፡ ለዚህም አሁን በስራ ላይ ባለው የፕሬስ ህግ መሰረት የማስታወቂያ ሚኒስቴር የምዝገባ ጥያቄ በቀረበለት በአንድ ወር ውስጥ ምዝገባ ካላከናወነ እና የማይመዘግብበትን ምክንያት ካልገለጸ አመልካቹ እንደተመዘገበ ይቆጠራል የሚለውን ድንጋጌ ለዋቢነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ተመሳሳይ ድንጋጌ በዚህ ረቂቅ ውስጥ ቢካተት የአመልካቾችን መብት ከመጠበቅ ረገድ የተሻለ ይሆናል፡፡

በረቂቅ ህጉ ላይ በምዝገባ እና ፈቃድ መካከል ያለው ልዩነት በግልጽ አልተቀመጠም፡፡ ምዝገባ በኤጀንሲው የሚከናወንና ለድርጅቱ ህጋዊ ሰውነት የሚያሰጥ ሲሆን ፈቃድ ደግሞ በዘርፍ አስተዳዳሪው ድርጅቱ አስፈላጊውን የቴክኒክ ብቃት እንዳሟላ ሲረጋገጥ የሚሰጥ ነው የሚባል ከሆነ ይህ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የአንቀጽ 73/2 አማርኛው ቅጂ «የሚከተሉት ሰነዶች ከምዝገባ ማመልከቻው ጋር ተያይዘው መቅረብ አለባቸው» የሚል ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ቢስተካከል፤ ኤጀንሲው ተጨማሪ ሰነዶችን ለመጠየቅ የተሰጠውን ሥልጣን ቢቻል ማስቀረት፤ ካልሆነ ደግሞ የሰነዶቹን ባህሪ የሚጠቁም ሃረግ በአገላለፁ ላይ ማስገባት ለአንቀፁ የተሻለ ግልፅነት ይሰጠዋል፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው ማመልከቻ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መመዝገብ እንዳለበት እና ለቀረበለት የምዝገባ ጥያቄ መልስ ባይሰጥ የሚኖረው ውጤት ቢገለጽ የተሻለ ነው፡፡ በምዝገባ እና በፈቃድ መካከል ያለው ልዩነት እና አስፈጻሚ አካላቱ እነማን እንደሆኑ ቢገለጽ ለአሰራር የተሻለ ይሆናል፡፡

**22. የምዝገባ ጥያቄን ስላለመቀበል (አንቀጽ 74)**

ይህ አንቀጽ የምዝገባ ጥያቄ የሚከለከልባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል፡፡ አንቀጽ 74/1 ኤጀንሲው አለመሟላታቸውን ካመነ ምዝገባ ለመከልከል የሚገደድባቸውን ምክንያቶች ሲያካትት አንቀጽ 74/2 ደግሞ ኤጀንሲው ምዝገባውን ለመከልከል የሚችልባቸውን ምክንያቶች ይዟል፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች ቢሆን ምዝገባን ለመከልከል የተቀመጡት የሚከተሉት ምክንያቶች በጥቅል/ሰፊ እና ግልጽ ባልሆነ ሁኔታ የተቀመጡና ተገቢ ላልሆነ አሰራር የተጋለጡ /**vague, open to subjective interpretation and abuse**/ ናቸው፡፡

**የመተዳደሪያ ደንብ በቂ አለመሆን፡-** ኤጀንሲው ምዝገባን ለመከልከል የሚገደድበት የመጀመሪያው ምክንያት የአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የመተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር በቂ አይደለም ብሎ ካመነ ነው፡፡ ከመነሻው «ኤጀንሲው ካመነ» የሚለው አባባል አጠራጣሪና ለትርጉም የተጋለጠ በመሆኑ ለረቂቅ ህጉ አፈጻጸም አስቸጋሪ ነው፡፡

በይበልጥ አስቸጋሪ የሚያደርገው ደግሞ ኤጀንሲው የአንድ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር የመተዳደሪያ ደንብ በአግባቡ ለማስተዳደር እና ለመቆጣጠር በቂ መሆኑን ወይም አለመሆኑን እንዴት እንደሚወስን አንቀጹ አያብራራም፡፡ ይህ እንኳን የሚቻል ቢሆን በዚህ የተነሳ ብቻ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንዳይመዘገብ መከልከሉ አግባብነት ያለው አይመስልም፡፡ ምክንያቱም ህጉ ራሱ

ለአስተዳደርና ቁጥጥር በቂ ድንጋጌዎችን ያስቀመጠ በመሆኑ የመተዳደሪያ ደንቡ ክፍተት ቢኖርበት እንኳ የህጉ አስገዳጅ አንቀጾች ክፍተቱን ሊሞሉ ይችላሉ፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ ጉድለት በሚያገኝበት ጊዜ ኤጀንሲው ምዝገባውን ከመከልከል ይልቅ መስራቾቹን አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርጉ ሊያዝ ይችላል፡፡ አመቺ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ከመፍጠር አኳያም ቢሆን የሚመረጠው ከክልከላ በፊት እንዲህ ዓይነቱ የቴክኒክ ድጋፍ እና የማማከር አገልግሎት መስጠቱ ይሆናል፡፡

**ህገ-ወጥነት ወይም የህዝብ ደህንነትና ፀጥታ፡-** አንቀጽ 74/1/ለ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ቢመዘገብ ለህገወጥ ዓላማ ወይም ለህዝብ ሰላም ተቃራኒ ለሆነ ዓላማ ሊውል ይችላል የሚያሰኝ ግምት ሲኖር ምዝገባው መከልከል እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ተቋም የሚመዘገብበት ዓላማ በመመስረቻ ፅሁፉ ውስጥ በግልፅ የሚቀመጥ ከመሆኑ አኳያ «የሚያሰኝ ግምት ሲኖር» የሚለው አባባል ምንን ለማመልከት እንደሆነ ግልጽ አይደለም፡፡ በግልፅ የተቀመጠው ዓላማ ህገወጥ ሆኖ ከተገኘ ክልከላው አግባብነት የሚኖረው ቢሆንም አንቀጹ ይህንን አስቦ የተቀረጸ አይመስልም፡፡

ኤጀንሲው ገና በመመዝገብ ላይ ያለ ድርጅት ለህገወጥ ዓላማ ሊውል እንደሚችል በምን መነሻ ሊገምት ይችላል? የአባላቱን መግለጫ በመመልከት ነው ወይስ በመካከላቸው ሊኖር የሚችል የምስጢር ስምምነትን በመገመት? ይህ ደግሞ ገና ባልተፈጸመ ተግባር በይሆናል ብቻ የዜጎችን መብት የመገደብ ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ በተጨማሪም የህዝብ ሰላም ማለት ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንደሚወሰን የተቀመጠ ነገር ባለመኖሩ ችግሩ እንኳን ተፈጥሯል ብሎ በርግጠኝነት ለመወሰን አስቸጋሪ ነው፡፡

**ኤጀንሲው ስልጣን የሌለው ሲሆን፡-** በአንቀጽ 74/1/ሀ ላይ ኤጀንሲው ሥልጣን የሌለው ሲሆን ምዝገባውን መከልከል እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ኤጀንሲው የተቋቋመው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራትን ለመቆጣጠር እንደመሆኑ በምን ሁኔታ ለመመዝገብ ሥልጣን እንደማይኖረው ግልፅ አይደለም፡፡ ስለዚህ የዚህን አንቀጽ ተፈፃሚነት ለማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የሰራተኞች ማህበር ለኤጀንሲው የምዝገባ ማመልከቻ ሊያቀርብበት የሚችልበትን ሁኔታ ለመገመት ያስቸግራል፡፡ በመሆኑም የዚህ አንቀጽ አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ አጅግ አጠራጣሪ ነው፡፡

**የአስተዳደር ደንቦች አለማሟላት፡-** አራተኛው ምዝገባ የመከልከያ ምክንያት በረቂቅ አዋጁ እና በአዋጁ መሰረት የሚወጡ ደንቦችን አለመከተል ነው፡፡ ይህም ቢሆን ረቂቅ አዋጁ ከምዝገባ ማመልከቻ ጋር መያያዝ ካለባቸው ሰነዶች ዝርዝር ውጭ የሚያስቀምጠው ቅድመ-ሁኔታ ካለመኖሩ አኳያ ግራ የሚያጋባ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህም አንቀጽ ተፈጻሚነት አጠያያቂ ነው፡፡

**የአባላት ዜግነት፡-** ሌላው የክልከላ ምክንያት ደግሞ በአንቀጽ 74/1/ሠ ላይ የተጠቀሰው ነው፡፡ የውጭ የሲቪል ማህበረሰብ ደርጅቶች ምዝገባ የሚከለከሉበት ምክንያት ግልፅ ካለመሆኑ በተጨማሪ ከገቢያቸው ከአስር በመቶ በላይ ከውጭ የሚያገኙ አገር-በቀል ድርጅቶች ላይም አሉታዊ ውጤት

ይኖረዋል፡፡ ተፈጻሚነቱ በውጭ ዜጎች በተመሰረቱ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ላይ ብቻ ቢሆንም እንኳን የውጭ ዜጎች የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዳያቋቁሙ የሚከለከሉበት ምክንያት ግልፅ ሆኖ አላ ገኘነውም፡፡ እንዲህ ያለው ክልከላ ከሕገ-መንግስቱ አንቀጽ 31 እና ያለማዳላትና የመደራጀት ነጻነትን ከሚመለከቱት የአለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጾች ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሰብዓዊ መብቶች ሰው በመሆናችን ብቻ የምናገኛቸው እንደመሆናቸው በዜግነት ወይም በዘር የተመሰረቱ አለመሆናቸው ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም የውጭ ዜጎች በሰውነታቸው ለህጋዊ አላማ የመደራጀት መብታቸውን መከልከል በዜግነት ላይ የተመሰረተ መድልዎ እንደመሆኑ ከብዙ አለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ጋር ይጋጫል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ክልከላ ከፖሊሲ አኳያም ድጋፍ የሚኖረው አይደለም፡፡ የውጭ ዜጎች ለበጎ አድራጎትና ለልማት ዓላማ ማህበር ቢመሰርቱ ጥቅሙ ለኢትዮጵያ ህዝቦች ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ አንቀጽ በተለያዩ አገሮች ዜጎች በኢትዮጵያ የተመሰረቱ የባህል ልውውጥ እና የወዳጅነት ማህበራትን ህጋዊ መሰረት የሚያሳጣ እንደመሆኑ አገሪቱ የተፈራረመቻቸውን የወዳጅነት ስምምነቶች የሚቃረን ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የአገሪቱን የዲፕሎማሲ ግንኙነት የማበላሸትና ኢንቬስትመንትን የማዳከም ውጤት ይኖረዋል፡፡ ስለዚህ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የፖለቲካ ባህሪ አላቸው ከሚል ግምት ካልተነሳ በቀር ይህ አንቀጽ ምንም መሰረት ያለው አይመስለንም፡፡

ምንም እንኳ አንቀጽ 74/2 የፍትህ ሚኒስትሩ ወይም የዘርፍ ሚኒስትሩ የውጭ ዜጎች ማህበራት እና የበጎ አድራጎት ድርጅት እንዲመሰርቱ በችሮታ መልክ ሊፈቅድ እንደሚችል ቢደነግግም የውጭ ዜጎችን መሰረታዊ መብት ወደ ችሮታ መቀየሩ የመብት መጣሱን አያስቀረውም፡፡ በውጤቱም የመደራጀት መብትን ለውጭ ዜጎች ከመርህ ይልቅ እንደ ልዩ ሁኔታ የሚሰጥ ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንቀጹ ግልፅ ያልሆነና ለመፈጸም የሚያስቸግር ነው፡፡ ለምሳሌ ይህ አንቀጽ ተፈጻሚ እንዲሆን ሁሉም መስራች አባላት የውጭ ዜጎች መሆን አለባቸው? ከመስራቾቹ መካከል ከፊሎቹ ኢትዮጵያውያን ቢሆኑስ? ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመፈለግ ወደ አንቀጽ 74/2 ብንመለስ ጉዳዩን ከማብራራት ይልቅ በኢትዮጵያውያንና በውጭ ዜጎች የተመሰረቱ ማህበራት (ድርጅቶችን ሳይጨምር) በአዋጅ እንደሚተዳደሩ ብቻ ያስቀምጣል፡፡ ቢሆን ቢሆን አንቀጹ የሚነግረን በውጭ ዜጎች የተመሰረቱ ማህበራት በሚኒስትሩ ፈቃድ ሊመዘገቡ እንደሚችሉ ብቻ ነው፡፡

ኤጀንሲው በነዚህ ሰፋፊና ግልጽ ያልሆኑ ምክንያቶች የሲቪል ማህበረሰብ ተቋማትን ምዝገባ እንዲከለክል ሥልጣን መስጠት ውጤቱ የዜጎችን የመደራጀት መብት መገደብ ነው፡፡ ይህ ክልከላ ለሚኒስትሩ በሚቀርብ አቤቱታ መሠረት የኤጀንሲው ውሳኔዎች እንደገና እንዲታዩ ከማድረግ በስተቀር በምዝገባ ክልከላ ላይ ለፍርድ ቤት ፍሬ ነገርን የተመለከተ ይግባኝ እንዳይቀርብ ከሚከለክለው አንቀጽ 118(3) ጋር በጣምራ ሲታይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን የእንቅስቃሴ አድማስ የሚያጠብ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን አስተዳደራዊ ክለሳ (administrative review) ጠቀሜታ ቢኖረውም በፍርድ ቤት ጉዳይን ማሳየት አለመቻል ህገመንግስታዊ እውቅና የተሰጠውን የመደራጀት መብት እና በአንቀጽ 38 የተቀመጠውን ፍትህ የማግኘት መብት የሚያሳጣ ነው፡፡ ፍርድ ቤቶችም በህገመንግስቱ አንቀጽ 9/3 ህገመንግስቱን ለማስፈጸምና የዜጎችን መሰረታዊ መብቶች ለመጠበቅ የተሰጣቸውን ኃላፊነትም ይቃረናል፡፡

አንቀጽ 74/3፡- ኤጀንሲው ፈቃድ ሊከለክልባቸው የሚችልባቸው ምክንያቶች በዚህ ንዑስ አንቀጽ ስር ተዘርዝረዋል፡፡ አብዛኞቹ ምክንያቶች ጠቅለል ባለ መልኩ የተቀመጡና በኤጀንሲው ባለስልጣኖች አለአግባብ ለመተግበር የተጋለጡ ናቸው፡፡ በእያንዳንዱ ንዑስ አንቀጽ ላይ ያለን አስተያየት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ከዚህ በፊት ከፈረሰ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ጋር ግንኙነት መኖሩ፡-** በአንቀጽ 74/3/ሀ መሰረት ለምዝገባ ያመለከተው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ከዚህ በፊት በአንቀጽ 105 ወይም በቀደመ ህግ መሰረት የፈረሰ ወይም ምዝገባ የተከለከለ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቅርንጫፍ ከሆነ ወይም ቅርበት ወይም ግንኙነት ያለው ከሆነ ኤጀንሲው ምዝገባውን ሊከለክል ይችላል፡፡ ይህ ድንጋጌ ምዝገባን ለመከልከል ግልጽነት የጎደለውና ለዘፈቀደ አፈጻጸም የተጋለጠ ምክንያት አስቀምጧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በአንቀጽ 105 መሰረት ከፈረሰ ድርጅት ጋር ቅርበት ወይም ግንኙነት አለ መባሉ ምዝገባ ለመከልከል ለምን በምክንያትነት እንደቀረበ ግልጽ አይደለም፡፡ ይህ ሰፊ ክልከላ ምን ያህል አግባብነት እንደሌለው ለመረዳት በአንቀጽ 105 ስር የተቀመጡትን የመፍረስ ምክንያቶች መመልከቱ ብቻ በቂ ነው፡፡

1. በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ግዜውን ጨርሶ ከሆነ
2. ዓላማውን አሳክቶ ከሆነ
3. በኤጀንሲው ከታዘዘ በኋላ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የመመስረቻ ሰነዱን ካላሻሻለ
4. የአባላት ቁጥር በህግ ከተደነገገው አነስተኛ ቁጥር በታች ከሆነ
5. የውጭ አገር የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በተቋቋመበት አገር ህግ መሰረት ሲፈርስ
6. የአዋጁን፤ የመመስረቻ ፅሁፉን ወይም በዚህ ህግ መሰረት በኤጀንሲው የወጡ መመሪያዎችን ሆን ብሎ የጣሰ ከሆነ
7. የተመዘገበው በማታለል ወይም በማጭበርበር ከሆነ
8. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ ህልውና መቀጠል ለህዝብ ጥቅም ተፃራሪ ከሆነ፡፡

እነዚህን ምክንያቶች እንዳሉ ብንወስዳቸው ከ1-6 ባሉት ምክንያቶች በዚህ አንቀጽ ስር ከፈረሰ ማህበር ወይም ድርጅት ጋር ቅርበት ወይም ግንኙነት ያለው የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ምዝገባ የሚከለከልበት ምክንያት ግራ ያጋባል፡፡ አባላቱ ከዚህ በፊት ስራውን አጠናቆ በፈረሰ ድርጅት ውስጥ ወይም የተቋቋመበት ዓላማ ተሳክቶ በፈረሰ ማህበር ውስጥ አባል ስለነበሩ ብቻ ኤጀንሲው ምዝገባ እንዲከለክል መፍቀዱ ምክንያቱ ምንድነው? የአባላቱ ቁጥር በህግ ከተደነገገው አነስተኛ ቁጥር በማነሱ ምክንያት ከፈረሰ ድርጅት ጋር ቅርበት ወይም ግንኙነት ያለው በመሆኑስ እንዳይመዘገብ ምን ይከለክለዋል?

በተጨማሪም ቅርበት ወይም ግንኙነት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግልፅ አይደለም፡፡ በሁለቱ መካከል ልዩነት ካለ ምንድነው? እንዲህ ያለው ቅርበትና ግንኙነትስ የሚረጋገጠው እንዴት ነው? ሁለቱም ድርጅቶች በምዝገባው ግዜ የሌሉ እንደመሆናቸው ግንኙነቱ በድርጅቶቹ መካከል ሊሆን አይችልም፡፡ በአንድ በኩል አመልካቹ ድርጅት ገና በመመስረት ላይ ነው፤ በሌላ በኩል ደግሞ የቀደመው ድርጅት በአንቀጽ 105 መሰረት ፈርሷል፡፡ በዚህ ሁኔታ ቅርበትና ግንኙነቱ በመስራቾቹ መካከል ነው? በመሪዎቹ መካከል ነው ወይስ በድርጅቶቹ ዓላማ? የቅርበቱና ግንኙነቱ ዓይነትስ ምን አይነት ነው? የስጋ ዝምድና ነው ወይስ የጋብቻ ወይስ ጓደኝነት ወይስ የንግድ? ረቂቅ ህጉ ለነዚህ

ጥያቄዎች ምላሽ ስለማይሰጥ የኤጀንሲው ኃላፊዎች አግባብነቱ በሚያጠራጥር ምክንያት ምዝገባ ሊከለክሉ ይችላሉ::

**በመስራቾቹ ወይም በመሪዎቹ መካከል ዝምድና መኖሩ፡-** አንቀጽ 74/3/ሐ በመስራቾቹ ወይም በመሪዎቹ መካከል የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ሲኖርና የድርጅቱ ንብረት ከዚህ የተነሳ ሊባክን ይችላል ብሎ ሲያምን ምዝገባ እንዲከለክል ይፈቅዳል:: ድርጅቱ ገና ባልተመዘገበበትና ስራ ባልጀመረበት ሁኔታ ዝምድና መኖሩ ወደ ግል ጥቅም ያመራል የሚለው የኤጀንሲው እምነት ከጥርጣሬ ያለፈ መሰረት አይኖረውም:: የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበርን ንብረት ለግል ጥቅም ማዋል ዝምድና ኖረም አልኖረ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰት ይችላል:: ስለዚህ የተሻለ አማራጭ የሚሆነው ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ ስርዓቶችንና ተቋሞችን መፍጠር እና አጥፍተው በሚገኙ ኃላፊዎችና መስራቾች ላይ በተጨባጭ መረጃ ላይ ተመስርቶ እርምጃ መውሰድ ይሆናል:: ምዝገባን መከልከል በነዚህ ሁኔታዎች እንደመፍትሄ ሊታይ የሚችል አይደለም:: ስለዚህ ይህ አንቀጽ ቢሰረዝ የተሻለ ይሆናል::

**የሚያሳስት፣ ለሞራል ተቃራኒ የሆነ ወይም የማይፈለግ ስያሜ፡-** በአንቀጽ 74/3/መ መሰረት የአንድ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት ስያሜ ከአላማው የራቀ፣ ህዝብን ሊያሳስት የሚችል፣ የሌላ በጎ አድራጎት ድርጅትን ስም የመሰለ፣ ለሞራል ተቃራኒ የሆነ፣ የማይፈለግ ወይም ህገወጥ ትርጉም ካለው ኤጀንሲው ምዝገባውን ሊከለክል ይችላል:: እነዚህ ምክንያቶች ግልጽ እና ምክንያታዊ ቢመስሉም በቅርበት ሲመረመሩ ብዙ ችግሮችና አሻሚ ሃረጎች የያዙ ናቸው:: በመርህ ደረጃ ኤጀንሲው ምዝገባውን ከመከልከል ይልቅ ችግሩን ያስነሳውን ስያሜ እንዲያስተካክል ለድርጅቱ መመሪያ እንዲሰጥ ማድረግ ቅድሚያ ሊሰጠው በተገባ ነበር:: ይህ መፍትሄ በረቂቁ አንቀጽ 79 ላይ ተቀምጧል:: ይህ መፍትሄ ተቀምጦ እያለ እነዚህ ጥቃቅን ጉዳዮች ምዝገባን ለመከልከል እንደ ምክንያት ሆነው መዘርዘራቸው አስፈላጊነቱ ግልጽ አይደለም::

አንዳንዶቹ ምክንያቶች ግልፅ ትርጉም ያልተሰጣቸው ናቸው:: ለምሳሌ «የሚያሳስት» ማለት ምን ማለት ነው? ከሌላ ድርጅት ስያሜ ጋር መመሳሰል እንደሆነ ለብቻው እንደ አንድ ምክንያት ተቀምጧል:: ስለ ድርጅቱ ስራ የሚያሳስት የሚለውም እንዲሁ:: ከነዚህ ውጭ የሚያሳስት ለሚለው ምን ትርጉም እንደሚሰጠው ለመገመት ያስቸግራል:: በተመሣሣይ መልኩ «የማይፈለግ» የሚለውም እጅግ ሰፊና አላስፈላጊ ምክንያት ነው:: አንድ ስያሜ አላስፈላጊ ሊባል የሚችለው ለሞራል ወይም ለህግ ተቃራኒ ሲሆን ነው:: እነዚህ ደግሞ ራሳቸውን ችለው ተለይተው ተቀምጠዋል:: ከነዚህ ውጭ በሆነ ምክንያት ስያሜው አላስፈላጊ ነው ብሎ ኤጀንሲው ምዝገባ እንዲከለክል ስልጣን መስጠት ለዘፈቀደ አሰራር መንገድ ይከፍታል::

**ቀጣይነት፡-** በአንቀጽ 74/3/ረ መሰረት የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱ በመተዳደሪያ ደንቡ ወይም በቂ ገንዘብ ስለሌለው ዓላማውን ለማሳካት የማይችል ሲሆን ኤጀንሲው ምዝገባ ለመከልከል ይችላል:: ኤጀንሲው የድርጅቱን ቀጣይነት ገና ከምዝገባው በፊት ሊተነብይ እንደሚችል ለመገመት ያዳግታል:: በቂ ገንዘብ አለመኖርን ምዝገባ ለመከልከል እንደምክንያት ማስቀመጡ ረቂቅ ህጉ በንግድ ድርጅት እና በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት መካከል ያለውን ልዩነት ያላገናዘበ ይመስላል:: የንግድ ድርጅቶች የገንዘባቸው ምንጭ መስራች አባላት ብቻ በመሆናቸው ስራ ከመጀመራቸው በፊት የተወሰነ ገንዘብ

እንዲያስቀምጡ ይጠየቃሉ። የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ግን የተለያዩ የገንዘብ ምንጮች አሉዋቸው። አብዛኛውን ጊዜ በተወሰነ የግዜ ገደብ የሚጠናቀቁ መርሃ ግብሮችን ለማስፈፀም ገንዘብ ከአባላት እና ከለጋሾች ሊጠይቁ ይችላሉ። ስለዚህ ተመዝግቦ ስራ ከጀመረም በኋላ ቢሆን አንድ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት በቂ ገንዘብ ያገኛል ወይም አያገኝም ብሎ መተንበይ ያስቸግራል።

የመመስረቻ ፅሁፉ በምን ሁኔታ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቱን ዓላማ ሊያሰናክል እንደሚችል ግልፅ አይደለም። ይህ የሚሆንበት አጋጣሚ ቢኖር እንኳ ኤጀንሲው ማድረግ ያለበት ድርጅቱ አስፈላጊውን ማሻሻያ እንዲያደርግ መምከር እንጂ ምዝገባ መከልከል አይገባውም። በተጨማሪም ረቂቅ ህጉ ዓላማን ለማሳካት ያለመቻል ብዙውን ጊዜ የሚመነጨው ከዓላማዎቹ አቀራረጽ እንጂ ድርጅቱ በኤጀንሲው የተዘጋጀለትን ሞዴል ተከትሎ ከሚያዘጋጀው የመመሥረቻ ፅሁፍ እንዳልሆነ ከግምት ውስጥ ያስገባ አይመስልም።

የመደራጀት መብት ሊገደብ የሚችለው በግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ ማህበራሰብ ውስጥ ተቀባይነት ባላቸው ምክንያቶች፣ ለህዝብ ጥቅም ሲባልና በአግባቡ በወጣ ህግ በተቀመጠው መሰረት ብቻ ነው። በረቂቅ ህጉ ውስጥ ምዝገባንና የምዝገባ ክልከላን በተመለከተ የሚከተሉት አላግባብ በኤጀንሲው ፍቃድ ላይ ለተመሰረተ ውሳኔ ተትተዋል።

- ተጨማሪ ሰነዶች ... <u>ኤጀንሲው የሚጠይቃቸው</u> (አንቀጽ 73/2/ረ)
- ሊቋቋም የታሰበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር መተዳደሪያ ደንብ ... <u>ለመምራትና ለመቆጣጠር በቂ ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር</u> (አንቀጽ 74/1/ሀ)
- ሊቋቋም የታሰበው የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር <u>ህገ-ወጥ ለሆነ፣ የህዝብን ሰላም ለሚያደፈርስ ወይም የኢትዮጵያን ደህንነትና መረጋጋት ለመጉዳት መጠቀሚያ ሊሆን ይችላል የሚያሰኝ ግምት ሲኖር</u> (አንቀጽ 74/1/ሀ)
- ... የስጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ኖሮ <u>በኤጀንሲው እምነት</u> የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ለግል ጥቅም ይውላል ተብሎ ሲገመት (አንቀጽ 74/3/ሐ)
- የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የሚመዘገብበት ስም ... <u>በኤጀንሲው እምነት የማይፈለግ፣ ከሞራል ወይም ከሕግ የሚቃረን ሲሆን</u> (አንቀጽ 74/3/መ)

የተሰመረባቸው ቃላትና ሃረጎች ማንኛውም ትርጓሜ እንዳልተሰጣቸውና በኤጀንሲው አተረጓጎም የሚወሰኑ በመሆናቸው ለተጣረሰ አፈፃፀም የተጋለጡ መሆናቸውን ልብ ይሏል።

**የማሻሻያ ሀሳብ፡-**

- አንቀጽ 74/1/ሀ፡- ይህ ንኡስ አንቀጽ በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የስራ አስፈጻሚ አካላት ለሚደረገው አመራርና ቁጥጥር ዝቅተኛ መመዘኛዎች በግልጽ ቢያስቀምጥ ወይም ንኡስ አንቀጹ ተሰርዞ የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የስራ አስፈጻሚ አካላት የተረጋገጠ የአመራር ግድፈት በሚፈጽሙበት ጊዜ ለሚጠየቁበት ሁኔታ ሌላ ቦታ ይካተት።

- አንቀጽ 74/1/ለ:- ይህ ድንጋጌ በወንጀለኛ መቅጫ ህግ በተመለከተው መሰረት የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ወይም ማህበሩ በህገ-ወጥ ተግባር የሚሳተፍ መሆኑን የመተዳደሪያ ደንቡ በግልጽ የሚያሳይ ከሆነ ምዝገባ ይከለከላል በሚል መልኩ ቢሻሻል::

- አንቀጽ 74/1/መ:- የማይታወቅ ተጨማሪ መለኪያ እንዲገባ መንገድ ስለሚከፍት ይህ ድንጋጌ ቢወጣ::

- አንቀጽ 74/1/ሠ:- የአንቀጹ ድንጋጌ «በውጭ አገር ህግ በውጭ ዜጎች የተቋቋሙ ማህበራት» በሚል ቢገደብ፣

- አንቀጽ 74/3/ሀ: በዚህ አንቀጽ ስር ምዝገባ የሚከለከልበት ሁኔታ ማህበሩ ህገወጥ ከሆነና ቢመዘገብ ወደ ህገወጥ ተግባር እንደሚያመራ ማንኛውም ምክንያታዊ ጥርጣሬ በሌለበት ሁኔታ ብቻ እንደሆነ ተገልጾ ቢሻሻል፣

- አንቀጽ 74/3/ለ:- በዚህ አንቀጽ ስር ምዝገባ የሚከለከልበት ምክንያት ስራ አስፈጻሚው በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት በዴሞክራሲያዊ መንገድ በጠቅላላ ጉባዔው የማይመረጥ ከሆነ ወይም በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ንብረቱን ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር ስልጣን ካልተሰጣቸው እና ከነዚህ በአንዱ ምክንያት ከማህበሩ አባላት መካከል 50 በመቶ የሚሆኑት ለኤጀንሲው ምዝገባውን እንዲከለክል ካመለከቱ በሚል ቢሻሻል፣

- አንቀጽ 74/3/ሐ:- ይህ አንቀጽ የአንድ ማህበር ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅት ህጋዊ አላማና ትክክለኛ አስተዳደር ህጋዊ ተቀባይነት ባላቸው መንገዶች ሊረጋገጥና ሊታወቅ እየቻለ ምዝገባን ለመከልከል አላስፈላጊና የዘፈቀደ ምክንያት ስለሚያስቀምጥ ቢሰረዝ ይመረጣል፣

- አንቀጽ 74/3/መ:- ይህ ንዑስ አንቀጽ ቢሰረዝ፣

- አንቀጽ 74/3/ሠ:- ይህ ንዑስ አንቀጽ ቢሰረዝ፣

- አንቀጽ 74/3/ረ:- ማህበሩ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ ከተመዘገበ በአንድ ዓመት ውስጥ በቂ ገንዘብ መሰብሰብና መንቀሳቀስ ካልቻሉ በራሱ ስለሚፈርስ ይህ ንዑስ አንቀጽ ቢሰረዝ፤ ማህበሩ ወይም የበጎ አድራጎት ድርጅቱ እንቅስቃሴውን ለመቀጠል መቻሉ ወይም አለመቻሉ አመታዊ የስራና የገንዘብ አጠቃቀም ሪፖርቱን ሲያቀርብ ሊመዘን ይችላል::

**የማሻሻያ** ሀሳብ:- የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች የመደራጀት መብት የግድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ በግልጽ ህግ ሊገደብ የሚችል መሰረታዊ መብት እንደሆነ ከግምት ውስጥ በማስገባት እንደገና ቢታዩ:: በተለይም:-

- ምዝገባ ለመከልከል የተቀመጡ ገደቦች ከሚያስጠብቁት ጥቅም ተነፃፃሪ ዎጋ አንፃር የዜጎችን መሰረታዊ መብቶች ለመገደብ አስፈላጊነታቸው ቢገመገም፣

- ለኤጀንሲው ሰፊ ስልጣን የሚሰጡ ሃረጎች ግልፅ በሆኑ መለኪያዎች ተተክተው ምዝገባ ሊከለከል የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ቀድሞ ለማወቅ በሚያስችል መልኩ አንቀፆቹ ቢታረሙ፣

- ኤጀንሲው ያልተሟሉ ሁኔታዎችን እንዲያሟሉ አመልካቾችን የሚጠይቅበት አግባብ በግልፅ ቢቀመጥ፣

በአጠቃላይ የዚህ አንቀጽ ይዘትና አገላለፅ ለህገመንግስቱ ድንጋጌዎች ሰፊ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ እንደገና ቢታዩ።

**24. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቅርንጫፍ (አንቀጽ 77)**

ይህ አንቀጽ ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቅርንጫፍ ለመክፈት የኤጀንሲውን ፈቃድ በቅድሚያ ማግኘት እንዳለበትና ፈቃድ ሊከለከል የሚችልባቸውን ምክንያቶች ይዘረዝራል። በመጨረሻም ያለፈቃድ የተቋቋመ ቅርንጫፍ እንደ ህገወጥ ድርጅት ወይም ማህበር እንደሚቆጠር ተደንግጓል። በተለይ በመመስረቻ ሰነዱ ላይ ቅርንጫፍ እንደሚኖረው የተገለፀ ከሆነ ቅድሚያ ፈቃድ የመጠየቁ አስፈላጊነት አጠያያቂ ነው። ለክልከላ የተቀመጡትም ምክንያቶች በቀላሉ ሊታረሙ የሚችሉ ይመስላሉ። በመጨረሻም አንቀጽ 77/3 ህጋዊ አላማ ባለው ድርጅት ወይም ማህበር ያለፈቃድ በተቋቋመው ቅርንጫፍ ምንም ዓይነት ወንጀል ሳይፈፀም ወደ ወንጀል ቅጣት የሚያመራበት ሁኔታ ይታያል።

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** በመመስረቻ ሰነዱ ላይ ቅርንጫፍ እንደሚኖረው የተገለፀ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ቅርንጫፍ መክፈቱን በተወሰነ የግዜ ገደብ የማስታወቅ ግዴታ ብቻ ቢኖርበት፣ ቅርንጫፍ ለመክፈት የቀረበን ጥያቄ ቅርንጫፉ የተሰጠው ስልጣን ሰፊ በመሆኑ ብቻ ከመከልከል እና ወደ ወንጀል ቅጣት ከመሄድ ይልቅ ድርጅቱ ወይም ማህበሩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ዕድል በሚሰጥ መልኩ ቢሻሻል፤ እንዲሁም ያለፈቃድ ቅርንጫፍ መክፈት በአስተዳዳራዊ እርምጃ፣ ቢቻል በማስጠንቀቂያ የሚታለፍ ቢሆን። በአማራጭ በአንቀፅ 77/3 ላይ የተቀመጠው ቅጣት በቅርጫፉ ወንጀል ከተፈፀመ ብቻ የሚጣል ሆኖ ቢታረም።

**25. ስያሜ፣ የስራ ቦታ ወይም መተዳደሪያ ደንብ ስለመለወጥ (አንቀጽ 78 - 80)**

እነዚህ አንቀፆች ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ ስያሜውን፣ የስራ ቦታውን ወይም የመተዳደሪያ ደንቡን መለወጥ፣ በምልክቶች መጠቀም እንደማይችል እና ኤጀንሲው ማንኛውም የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሜውን ወይም የመተዳደሪያ ደንቡን እንዲቀይር ሥልጣን ያለው መሆኑን ይደነግጋሉ። የእነዚህን አንቀፆች ድንጋጌ የጣሰ ድርጅት ወይም ማህበር እና የስራ ኃላፊዎቹ በአንቀጽ 78/2 እና 80/3 መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ይጣልባቸዋል።

ከመነሻው የማህበራት በውስጥ ጉዳያቸው የመወሰን ነጻነት የመደራጀት መብት አንዱ መገለጫ እንደመሆኑ ስያሜ፣ የስራ ቦታን እና የመተዳደሪያ ደንብን ለመለወጥ ቅድሚያ ፈቃድ ማስፈለጉ ከህገመንግስታዊ ድንጋጌዎች ጋር የተጣጣመ መሆኑ ያጠያይቃል። ምንአልባት ለህግ ተቃራኒ አለመሆናቸውን ከማረጋገጥ ውጭ በስያሜና በመተዳደሪያ ደንብ ጉዳይ ኤጀንሲው የፈቃጅነት ስልጣን ሊኖረው ባልተገባ ነበር። የስራ ቦታ ለውጥንም ቢሆን አዲሱን የስራ ቦታ ከማወቅ ያለፈ

ኤጀንሲው ፈቃድና ከልካይ መሆኑ ግልፅ ጠቀሜታ ያለው አይመስልም፡፡ ይልቁንም ኤጀንሲው እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር እየተቆጣጠረ አቅሙን በአግባቡ መጠቀም እንዳይችል ያደርገዋል፡፡ ከዚያም አልፎ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ኤጀንሲው ለመወሰን የተሰጠው ሥልጣን «በኤጀንሲው አመለካከት» «በኤጀንሲው እምነት» እና «ግምት» በሚሉ ቃላትና ሃረጎች የተገለፀ መሆኑ በድርጅቶችና ማህበራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገባ በር ይከፍታል፡፡ በመጨረሻም በአንቀጽ 78/2 እና 80/3 መሰረት በሚወጣ ደንብ የሚጣለው አስተዳደራዊ ቅጣት ድርጊቱ በሦስተኛ ወገን ላይ ወይም በሌላ ጥቅም ላይ ጉዳት ባያደርስም ተግባራዊ የሚደረግ ይመስላል፡፡

> *የማሻሻያ ሀሳብ፡- የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስያሜውን፣ የስራ ቦታውን ወይም የመተዳደሪያ ደንቡን ሲለውጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለኤጀንሲው እንዲያሳውቅና በመሰረታዊ ሰነዶች ላይ የተደረገ ለውጥን በሚመለከት አዲሱን ሰነድ የመስጠት ግዴታ ቢጣልበት፤ ይህንን ማድረግ የሚያስቸግር እንኳ ሆኖ ቢገኝ ግዴታው ፈቃድ ከመጠየቅ ይልቅ ቀድሞ ማሳወቅ ቢሆንና የሚጎዳ ሦስተኛ ወገን ወይም ጥቅም መኖሩን ሲያረጋግጥ ብቻ ኤጀንሲው ጣልቃ የሚገባበት አኳኋን ቢታሰብ የተሻለ የህገመንግስቱ ድንጋጌዎችን የሚያስፈፅም ይሆናል፡፡ በአንቀፆቹ የተካተቱ አሻሚ ትርጉም ሊሰጣቸው የሚችሉ ቃላትና ሃረጎች በግልፅ ቃላት ቢተኩ ወይም የኤጀንሲውን ሥልጣን በሚወስን መልኩ ቢብራሩ፡፡ በአንቀጽ 78/2 እና 80/3 የተቀመጡት ቅጣቶች አስፈላጊነት ጉዳዮቹ የተቋማቱ የውስጥ ጉዳይ ከመሆናቸውና የሦስተኛ ወገኖችን ጥቅም የሚያስጠብቁ ህግጋት ከመኖራቸው አኳያ በድጋሚ ቢታዩ፡፡ እንዲሁም በነዚህ አንቀፆች መሰረት አስተዳደራዊ ቅጣት ከመወሰዱ በፊት ማስጠንቀቂያ የሚሰጥበት አግባብ ቢኖርና የተጠቀሰው ደንብም በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚወጣ መሆኑ በግልፅ ቢቀመጥ፡፡*

## 26. ሕገ ወጥ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ወይም ማህበራት (አንቀጽ 82 - 85)

እነዚህ አንቀፆች በአዋጁ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ያልተመዘገበ ድርጅት ወይም ማህበር ህገወጥ ተደርጎ እንደሚወሰድ እና ባልተመዘገበ ድርጅት ወይም ማህበር ውስጥ መስራት፣ ማስተዳደር፣ ስብሰባ እንዲያደርግ መፍቀድ፣ ወይም መረጃዎቹን ማሰራጨት በእስር ወይም በገንዘብ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋሉ፡፡

የነዚህ አንቀጾች እንደምታ ያልተመዘገቡ ማህበራትንና ቡድኖችን መከልከል ነው፡፡ በሌላ አባባል የዜጎች የመደራጀት መብት ተግባራዊ የሚሆነው በኤጀንሲው ህጋዊ እውቅና ሲሰጠው ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ መሰረታዊ መብቶች የማንንም ፈቃድ የማይጠይቁና የማይገሰሱ መሆናቸው ሲታሰብ የህገመንግስቱንም ሆነ ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶች ድንጋጌዎችንም ሆነ መንፈስ የሚቃረን ገደብ ነው፡፡ በተለይም በአንቀጽ 82/1 ላይ «እንደ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሲሰራ ቢገኝ» የሚለው አገላለፅ ሰፊ ትርጉም ሊሰጠው የሚችል በመሆኑ ዘመናት ያስቆጠሩና የኢትዮጵያውያን መገለጫ የሆኑ የመረዳጃ ማህበራትን ጨምሮ ሁሉንም ያልተመዘገቡ ቡድኖች የሚከለክል ይመስላል፡፡ እነዚህ ቡድኖች በምስጢር እስካልተንቀሳቀሱ ወይም ህገወጥ ዓላማ እስካልኖራቸው ድረስ የሚከለከሉበት ወይም በህገወጥነት የሚፈረጁበት ምክንያት ሊኖር አይገባም፡፡

ባልተመዘገቡ ማህበራት በማንኛውም ደረጃ መሳተፍን በተመለከተ የዜጎችን የመሰብሰብና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብት ታሳቢ ተደርጎ በግልፅ ህገወጥ የሆነ ዓላማ ያለው እስካልሆነ ድረስ የሚከለከልበት ብሎም ወንጀል የሚደረግበት አግባብ ግልፅ አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አንድ ግለሰብ ያልተመዘገበን ማህበር መረጃ ማሳተሙ ወይም ማሰራጨቱ የመረጃው ይዘት ከግምት ውስጥ ሳይገባ ህገወጥ ተደርጎ መወሰዱ መረጃ የመያዝና የማሰራጨት መብትን በግርድፉ የመከልከል ውጤት ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ልገሳ ወይም አስተዋጽኦ ለማድረግ ቃል መግባትን ጨምሮ ባልተመዘገበ ድርጅት ወይም ማህበር እንቅስቃሴዎች በማንኛውም መልኩ መሳተፍ ወይም መደገፍ በእነዚህ አንቀፆች ወንጀል ተደርጓል፡፡ በተለይም ለምዝገባ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ከማጠሩና ቅድመ-ሁኔታዎች ከአባላት አቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች ላይሟሉ ከመቻላቸው አንጻር በተለይ በመመስረት ላይ ባሉ ማህበራት አባላት ላይ የሚኖረው እንደምታ በአግባቡ ትኩረት የተሰጠው አይመስልም፡፡

> የማሻሻያ ሀሳብ፡- ምዝገባ ከአስገዳጅ ቅድመ-ሁኔታ ይልቅ ለማህበራት ጠቀሜታ ያለው ሆኖ ቢታሰብና አለመመዝገብ ከመንግስት አካላት ጋር ከመተባባር፣ በተወሰኑ መስኮች ከመስማራት፣ ወዘተ … ተደርጎ ቢቀረጽ እና ረቂቅ ህጉ ፈቃድ በሚያስፈልጋቸው እና በማያስፈልጋቸው ማህበራት መካከል ልዩነት ቢያደርግ ከህገመንግስቱ ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በአንቀጾቹ ውስጥ ወንጀል የተደረጉት ድርጊቶች ከዜጎች የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ የመረጃ እና ሌሎች መብቶች አኳያ እንደገና መገምገም ያስፈልጋል፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ከወንጀል ህግ ፅንሰ-ሃሳቦችና ከፍትህ መርሆዎች አኳያ የድርጊቶቹ ዓላማና ይዘት ከግምት ውስጥ በገባ መልኩ ክልከላዎቹና ቅጣቶቹ እንደገና መታየት ያስፈልጋቸዋል፡፡

**27. የፈቃድና የምዝገባ ሰርተፊኬት ስለማደስ (አንቀጽ 86)**

ይህ አንቀጽ የፈቃድና የምዝገባ ሰርቲፊኬት በየአመቱ እንደሚታደስ ይገልፃል፡፡ በአንድ በኩል አስፈለጊዎቹ ሰነዶች ተሟልተው መቅረባቸው ከተረጋገጠ እድሳቱ እንደሚፈጸም መደንገጉ እንደ ጠንካራ ጎን ሊወሰድ ይችላል፡፡ እንዲሁም ከአጠቃላይ ገቢው ከሰማንያ በመቶ በላይ ለተቋቋመበት ዓላማ ያዋለ ድርጅት ከመንግስት ማበረታቻ ሊደረግለት እንደሚችል ማሰቀመጡ የሚደገፍ በጎ ሃሳብ ነው፡፡

በሌላ በኩል ግን እድሳቱ በየአመቱ የሚደረግ መሆኑ በተለይ አሁን ካለው አሰራር ጋር ሲነፃፀር ወደኋላ እንደመመለስ ሊታይ ይችላል፡፡ ለእድሳት ዋነኛው መመዘኛ የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ እንደመሆኑም አመታዊ የፈቃድና የምዝገባ ዕድሳት የሚኖረው ፋይዳ ግልፅ አይደለም፡፡

> የማሻሻያ ሀሳብ፡- አስፈላጊ ሪፖርቶች እስከቀረቡ ድረስ እድሳቱ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚሆን ጊዜ ቢደረግ በቂ እና ለአሰራርም የተሻለ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሰባት:- ስለ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሒሳብና ሪፖርቶች**

**28. የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ (አንቀፅ 87)**

አንቀጽ 87/3 የለጋሹ ማንነት ሳይታወቅ የሚደረግ ልገሳን ይከለክላል:: አያይዞም ድርጅቶችና ማህበራት የለጋሾችን ማንነት የሚያመለክቱ መዝገቦች እንዲይዙ ያዛል:: የዚህ ክልከላ ዓላማ ግልጽ ካለመሆኑና ትኩረቱም ስለለጋሹ መረጃ ማግኘት ላይ ከመሆኑ ባሻገር የለጋሾችን የግል መረጃ ያለበቂ ምክንያት የሚጠይቅ ይመስላል:: በተጨማሪም የሲቪል ማህበረሰብ ሊያገኝ የሚችለውን ድጋፍ የሚቀንስና የበጎ አድራጎት ልምድን የሚያዳክም ውጤት ሊያመጣ ይችላል::

> **የማሻሻያ ሀሳብ:-** የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ባልታወቀ ለጋሽ የተደረገ ስጦታን እንዳይቀበሉ ከመከልከል ጀርባ ያለው የፖሊሲ ወይም አስተዳደራዊ ምክንያት በድጋሚ ቢታይ:: ክልከላው አግባብነት ያለው ሆኖ ቢገኝ እንኳን እንዲህ ዓይነቱ ልገሳ ቢደረግላቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው በግልፅ ቢቀመጥ::

**29. ዓመታዊ የሂሳብ ምርመራ ስለማድረግ (አንቀጽ 89)**

በአንቀጽ 89/3 ላይ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ማንኛውም የሂሳብ ምርመራ ኤጀንሲው በሚሾመው በውስጥ ወይም በውጭ ኦዲተር ሊደረግ እንደሚችል ይደነግጋል:: ይህ በምን ምክንያት እንደሚደረግ ወይም ወጪውን የሚሸፍነው ማን እንደሆነ ሳይገለፅ በደፈናው ለሚኒስትሩና ለኤጀንሲው የተተወ ይመስላል::

ቀጥሎም በአንቀጽ 89/4 ኤጀንሲው ሂሳቡ በውጭ ኦዲተር መመርመሩ የተሻለ መስሎ ከታየው ኦዲተሩን ሊሾም እንደሚችል እና በአንቀፅ 89/5 መሰረት ወጪው በድርጅቱ ወይም ማህበሩ እንደሚሸፈን ይደነግጋል:: ይህ እንግዲህ የሚሆነው ድርጅቱ ወይም ማህበሩ ገቢው ከብር አንድ መቶ ሺህ በታች በመሆኑ በአንቀጽ 89/2 ስር በውጭ ኦዲተር ማስመርመር ግዴታ ባይኖርበትም ጭምር ይመስላል::

> **የማሻሻያ ሀሳብ:-** ኤጀንሲው የውጭ ኦዲተር የሚሾምበት እና የሂሳብ ምርመራ የሚያስደርግበት ምክንያት በግልጽ ቢዘረዘር:: በአንቀጽ 89/3 መሰረት ለሚደረገው ምርመራ ወጪውን ማን እንደሚሸፍን ግልፅ ቢደረግ:: ባሉበት ሁኔታ አንቀጽ 89/3 እና 89/4 ተደራራቢነት ያላቸው በመሆኑ እንደገና ታይተው ቢዋሃዱ ወይም አንዳቸው ቢሰረዙ::

**30. አመታዊ ሪፖርት (አንቀጽ 90)**

በዚህ አንቀጽ ንዑስ ቁጥር 2 ላይ አመታዊ ሪፖርት የሚቀርብበት ጊዜ በአማርኛው ቅጂ በሁለት ወር በእንግሊዝኛው ደግሞ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ተብሎ ተቀምጧል:: የሆነ ሆኖ በሁለቱም ቅጂዎች የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በተለይ ብዙ ቅርንጫፎች ላሉት ወይም ሰፊ እንቅስቃሴ ለሚያደርግ ድርጅት ወይም ማህበር በቂ አይደለም:: የበጀት ዓመቱ ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ

በተለይ በውጭ ኦዲተር ሂሳብን አስመርምሮ ሪፖርት ማቅረብ የማይቻልበት ከአቅም በላይ የሆነ አጋጣሚ መከሰቱም የሚቀር አይሆንም፡፡ በነዚህ ግዜያት በንዑስ ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰው አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰዱ አግባብ አይመስልም፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፡-** በቅጂዎቹ መካከል ያለው መጣረስ ሊስተካከልና ኦዲተሮች እንዳይጣደፉ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ የጊዜ ገደቡ ቢታይ፡፡ በተለይ በውጭ ኦዲተር ሂሳባቸውን የማስመርመር ግዴታ ላለባቸው ድርጅቶችና ማህበራት ረዘም ያለ ጊዜ ቢሰጥ ወይም የእያንዳንዱን ተቋም ሁኔታ እያገናዘበ ግዜው የሚራዘምበት አሰራር ቢታሰብ የተሻለ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ከአቅም በላይ የሆነ አጋጣሚ ሲፈጠርም አስተዳደራዊ እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ሌሎች አማራጮች የሚታዩበት ሁኔታ መኖሩም ጠቃሚ ይሆናል፡፡

**31. የባንክ ሂሳብ ስለማስታወቅ (አንቀጽ 93)**

አንቀጽ 93/1 የባንክ ሂሳብን ከሚፈለገው ዝርዝር ጋር በየጊዜው የማሳወቅ ግዴታ ይጥላል፡፡ ይህንን አለማድረግ ደግሞ አስተዳደራዊ ቅጣትን ያስከትላል፡፡ እዚህ ላይ በየጊዜው የሚለው ቃል አስፈላጊነቱም ሆነ ትርጉሙ ግልፅ አይደለም፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የባንክ ሂሳብ የማሳወቅ ግዴታ ቢቻል ከአመታዊ የፋይናንስ አጠቃቀም ሪፖርት ጋር ቢሆን፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ አዲስ የባንክ ሂሳብ ሲከፈት፣ ለውጥ ሲደረግ፣ ከኤጀንሲው ጥያቄ ሲቀርብ ወይንም በታወቀ የግዜ ገደብ የሚደረግ ቢሆን የተሻለ አግባብና ግልፅ ይሆናል፡፡

**ክፍል ስምንት፡- የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራትን ስለመቆጣጠር**

**32. ምርመራ የማድረግ ስልጣን (አንቀጽ 94)**

አንቀጽ 94/1 ለኤጀንሲው ላልተገለጸ ጠቅላላ ወይም ልዩ ዓላማ በአንድ ወይም በብዙ ወይም በሁሉም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ላይ ምርመራ የማድረግ ስልጣን ይሰጣል፡፡ ለዚህም በአንቀጽ 94/2፣ 4 እና 5 በስራ መሪዎች እና ሰራተኞች ላይ በአስተዳደራዊ ቅጣት የተደገፈ ግዴታ ይጥላል፡፡ ይህ ሥልጣን እና ተነፃፃሪ ግዴታ የተቀመጠው ማንኛውንም ምክንያት በማይሰጥና ገደብ በሌለበት የዘፈቀደ አገላለጽ ሆኖ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ከመልካም አስተዳደር መርሆዎች በተለይም ከግልፅነትና ተጠያቂነት አኳያ አግባብነቱ ያጠያይቃል፡፡

**የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ኤጀንሲው ምረመራ የሚያደርግበት ምክንያት እና የምርመራውን ሂደት በተመለከተ ቢያንስ ጠቋሚ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢካተቱ፡፡ በንዑስ አንቀጽ 4 ላይ የተቀመጠው አገላለፅም ከአቅም በላይ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ቢስተካከል፡፡

**33. ሠነዶች እንዲቀርቡ የማዘዝና ሪከርዶች እንዲመረመሩ የማድረግ ስልጣን (አንቀጽ 95)**

የዚህ አንቀጽ ይዘት ከአንቀጽ 94 ጋር ተደራራቢ ወይም ድግግሞሽ ነው፡፡ ልዩነቱ ኤጀንሲው ሰነዶችን በነፃ እንደሚያገኝ መግለፁ ላይ ብቻ ሆኖ ይታያል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ከላይ ለአንቀጽ 95 የተሰጠው አስተያየት ታሳቢ ቢደረግ፡፡

**34. ስብሰባዎችን ስለማስታወቅ (አንቀፅ 96 እና 97)**

እነዚህ አንቀጾች ጠቅላላ ጉባዔ የሚካሄድ መሆኑን ቀድሞ ስለማሳወቅ እና በዚህ ጉባዔ ላይ በኤጀንሲው ወይም በዘርፍ አስተዳዳሪው የሚወከል ሰው መሳተፍ የሚችል መሆኑን ይደነግጋሉ፡፡ ከመነሻው ጠቅላላ ጉባዔ የውስጥ ጉዳይ ከመሆኑና ቃለ-ጉባዔውም ለኤጀንሲው የሚላክ ከመሆኑ አንፃር የነዚህ ድንጋጌዎች አስፈላጊነትም ሆነ አግባብነት አጠራጣሪ ነው፡፡ ከዚህ አልፎም በማህበራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ ቁጥጥር ለማድረግ የሚሰጥ አስተዳደራዊ ስልጣን እንደዚህ በሰፊው ያለገደብ ሲሆንና ለማንም ሰው በውክልና የሚተላለፍ ሲሆን መልካም ገፅታ አይኖረውም፡፡ ይልቁንም የሚወከለው ሰው የፖሊስ መኮንን መሆኑ ወንጀል ይፈፀማል የሚል ግምትን እና ወንጀልን ከመከላከል ያለፈ ወንጀል አለመፈፀሙን የማረጋገጥ እንደምታ ይሰጠዋል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** እነዚህ አንቀጾች አስፈላጊነታቸውና አግባብነታቸው እንደገና ሊመረመርና ቢቻል ሊሰረዙ ይገባል፡፡

**35. አስተዳደራዊ ወጪዎችን የመቆጣጠር ስልጣን (አንቀጽ 101)**

በማንኛውም መስሪያ ቤት ውስጥ አስተዳደራዊ ወጭዎችን ማሳነስ ጠቃሚ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በተለይም በበጎ አድራጎት ተቋማት በተቻለ መጠን ከፍተኛው የገቢ መጠን ለዋነኛው ዓላማ መዋሉ የሚደገፍና የሚበረታታ ነው፡፡ በዚሁ መንፈስ ይመስላል ይህ አንቀጽ የማንኛውም የበጎ አድራጎት ተቋም አስተዳደራዊ ወጪ የሃብቱን ሰላሳ በመቶ እንዳይበልጥ ይደነግጋል፡፡ ከዚያም አልፎ ለኤጀንሲውና ለዘርፍ አስተዳዳሪው ትዕዛዝ የመስጠትና የመከታተል ሥልጣን ይሰጣል፡፡ የአንቀፁ መንፈስ መልካም ሆኖ ሳለ አፃፃፉ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡ በመጀመሪያ የአንድ ተቋም አስተዳደራዊ ወጪ ምን ማለት እንደሆነ አልተገለፀም፡፡ በደርጅቶች ወይም ማህበራት መካከል ያለው የባህሪ ልዩነትና በአስተዳደራዊ ወጭዎች ላይ የሚያሳድረው ተፅእኖም ከግምት ውስጥ ሳይገባ በቁርጥ ተወስኗል፡፡ ለኤጀንሲውና ለዘርፍ አስተዳዳሪው የተሰጠው ሥልጣንም በደፈናው የተገለፀ ነው፡፡ በመጨረሻም ይህንን ግዴታ መፈፀም የአቅም እና የሌሎች ታሳቢዎች ውጤት መሆኑ ሳይገናዘብ አስተዳደራዊ ቅጣት የሚጣልበት ሁኔታ ተቀምጧል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ይህ አንቀጽ በጠቅላላው እና በሚያስቀጣ መልኩ ከሚቀመጥ ኤጀንሲውና የዘርፍ አስተዳዳሪው የሲቪል ማህበራትን ለማጠናከር ሊጫወቱት የሚገባው ሚና ከግምት ውስጥ ገብቶ በአዎንታዊ አገላለፅ ቢቀመጥ የተሻለ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ ቅጣት

ማስቀመጡ አስፈላጊ ሆኖ ቢገኝ እንኳ የተቋማትን አቅም እና ባህሪ ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ቢሆን የተሻለ ይሆናል።

**36. የንብረት ጥበቃ (አንቀጽ 103)**

ኤጀንሲው ተገቢ ያልሆነ የስራ አመራር ወይም ድርጊት መፈፀሙን ሲያምን የተለያዩ እርምጃዎችን ለመውሰድ በዚህ አንቀፅ ሥልጣን ተሰጥቶታል። እነዚህም ኃላፊዎችን ከስራ ማንሳት፣ መሾምና ስልጣናቸውን መውሰድ፤ አልፎ ተርፎም ባልተገለጸ መንገድ አስተዳደሩ ሥርዓት እንዲይዝ ማድረግን ይጨምራሉ። ይህ ስልጣን የሚጠይቀው መለኪያ ኤጀንሲው የድርጅቱን ወይም የማህበሩን ንብረት ለመጠበቅ አስፈላጊ ነው ብሎ ማመኑ ብቻ ነው።

የአንድ በጎ አድራጎት ተቋም ንብረት በአስተዳደር ጉድለት መባከን የሌለበት መሆኑ የማይካድ ቢሆንም በዚህ አንቀጽ ለኤጀንሲው የተሰጠው ስልጣን አለቅጥ የሰፋና ያለ ግልፅ በቂ ምክንያት የሚተገበር ይመስላል። በቂ ምክንያት ባለበት ሁኔታ እንኳን በማህበሩ የውስጥ አሰራር ችግሮች እንዲታረሙ ለማድረግ ቅድሚያ አልተሰጠም። የዚህ አንቀጽ መንፈስ የራሱኑ ንኡስ ቁጥር 2 የሚቃረንም ሆኖ ይታያል።

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የዚህ አንቀጽ ይዘትና አቀራረብ እጅግ አስፈላጊ ሲሆንና ሌሎች አማራጮች ተሞክረው ውጤት ካላመጡ ብቻ በግልፅ በተደነገጉ ምክንያቶች ኤጀንሲው የማህበራቱን ንብረት ለመጠበቅ በተወሰነ መልኩ ጣልቃ እንደሚገባ በሚገልፅ መልኩ ቢከለሱ። ከተቻለም አጣዳፊነት ያለውና መልሶ ሊስተካከል የማይችል ጥፋት የሚከሰት መሆኑ በአግባቡ ካልተረጋገጠ በቀር ይህ ሥልጣን በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የሚፈፀም ቢሆን።

**37. የስራ መሪዎችን ስላ ማንሳትና መተካት (አንቀጽ 104)**

ይህ አንቀጽ ኤጀንሲው የስራ መሪዎችን ወይም ወኪሎችን ሊያነሳና ሊተካ የሚችልበትን ሁኔታና ሥልጣን ይደነግጋል። ይህ ሥልጣን የማህበሩን ንብረት ለባለአደራዎች እስከመስጠት የዘለቀ ሰፊ ስልጣን ከመሆኑ በተጨማሪ በተለይ ተጨማሪ የስራ ወኪል ወይም መሪ የሚመድብበት ምክንያት በኤጀንሲው የሚወሰን ሆኖ ይታያል። በሁሉም አማራጮች በማህበሩ የውስጥ አሰራር በኤጀንሲው አነሳሽነትም ቢሆን ችግሮች የሚፈቱበት መንገድ ቅድሚያ አልተሰጠውም። በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ በማህበሩ ኃላፊዎች ላይ ችግር መኖሩ ሳይረጋገጥ ተጨማሪ ኃላፊ የሚሾምበት አግባብም ተደንግጓል።

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ለአንቀጽ 103 የተሰጠው አስተያየት ለዚህም አንቀጽ ታሳቢ ቢደረግ።

**38. የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ስለመሰረዝ (አንቀጽ 105)**

አንቀጽ 105 የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ሰለሚሰረዝበት ሁኔታ የሚደነግግ ሲሆን ለዚህም የተለያዩ ምክንያቶችን ያስቀምጣል። ከነዚህም ውስጥ በኤጀንሲው ግምት «ለህዝብ ጥቅም ተፃራሪ» ከሆነ፣ መተዳደሪያ ደንቡን እንዲያሻሽል መመሪያ ተሰጥቶት በግዜ ገደብ ውስጥ ካላሻሻለ፣

እና የራሱን የመተዳደሪያ ደንብ ከጣሰ የሚሉ ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች መሟላታቸው የሚወሰነው ደግሞ በኤጀንሲው በራሱ ነው፡፡ በተጨማሪም የአባላት ቁጥር ከአነስተኛው በታች መውረድ እና የመስራቾች ወይም ኃላፊዎችን ጥፋት መሰረት በማድረግ የሚሰረዝባቸው ሁኔታዎችም ተደነግገዋል፡፡ የነዚህ ሁሉ ድምር ውጤት አግባብነት ያላቸው መሆኑ የሚያጠራጥሩ ምክንያቶች መካተታቸውን እና የኤጀንሲው ስልጣን ከመጠን አልፎ የሰፋ መሆኑን ያሳያል፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** አንድ ማህበር የሚሰረዝበት ምክንያት በህጉ በዝርዝር ሊወሰኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች ውስጥ ዋነኛው በመሆኑ ይህ አንቀጽ ያካተታቸው ግርድፍና ለትርጉም የተጋለጡ ቃላትና ሃረጎች ግልጽ ሊደረጉ ይገባል፡፡ የኤጀንሲው ስልጣንም በጠባቡ የሚሰጥና በፍርድ ቤት ሂደት ሲፀድቅ ብቻ ተፈፃሚ የሚሆን መሆን አለበት፡፡ ቢቻል አንድን ማህበር የማፍረስ ጉዳይ በተቻለ መጠን የፍርድ ቤት ብቻ ስልጣን ቢሆን ይመረጣል፡፡

### 39. ፍርድ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን ወይም ማህበራትን ስለሚያፈርስበት ሁኔታ (አንቀጽ 106)

ይህ አንቀጽ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የበጎ አድራጎት ድርጅትን ወይም ማህበርን የሚያፈርስበትን ሁኔታ ይመለከታል፡፡ ከርዕሱ ጀምሮ ፍርድ ቤት አንድን ማህበር «በማፍረስ» እንጂ «በመሰረዝ» ውሳኔ ስልጣን የሌለው ይመስላል፡፡ የንዑስ አንቀጽ 1 አገላለፅም ተመሣሣይ ትርጓሜ የሚያሰጥ ይመስላል፡፡ የረቂቅ አዋጁ አንቀፅ 118/3 ለፍርድ ቤት የሚቀርብ አቤቱታ «የሕግ ጥያቄን» ብቻ የሚመለከት መሆኑን ከመደንገጉ አንፃር በዚህ አንቀጽ የፍርድ ቤት ሚና የኤጀንሲውን ብሎም የሚኒስትሩን ውሳኔ ከማፅደቅ ያለፈ አይመስልም፡፡ ይህ ደግሞ የህግ የበላይነትን ብሎም የፍርድ ቤቶችን ተፈጥሯዊ ስልጣን የሚጋፋ ውጤት ይኖረዋል፡፡ በተለይም ጉዳዩ መሰረታዊ የዜጎች መብቶችን የሚመለከት መሆኑ ሲታሰብ የዚህን አንቀጽ አግባብነት እና ህገመንግስታዊነት መጠየቅ የግድ ይሆናል፡፡ የዚህ አንቀጽ ይዘት ከሌሎቹ አንቀጾች ጋር ተጣምሮ ሲታይ የዜጎች የመደራጀት መብት በኤጀንሲው ብሎም በሚኒስትሩ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እና በአስተዳደራዊ ውሳኔ ብቻ ሊከለከል የሚችል ነው የሚል እንደምታ አለው፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** መሰረታዊ የዜጎች መብቶችን፣ የህግ የበላይነትን እንዲሁም የፍርድ ቤቶችን ተፈጥሯዊ ስልጣን እና የስልጣን ነፃነት ከመጠበቅ አኳያ በዚህ አንቀጽ ለፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሱን ሚና በጥልቀት በድጋሚ ሊታይ ይገባል፡፡ ከአስተዳደር ተቋማት ተጠያቂነት እና ለህግ ተገዢነት አኳያም በማየት አስተዳደራዊ ውሳኔዎች በፍርድ ቤት የሚከለሱበት አግባብ ሊቀመጥ ይገባል፡፡ስለሆነም ማህበራትና በአድን የማፍረስ ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ሆኖ ኤጀንሲው ማህበራትን ከመሰረዝ ይልቅ የማፍረስ ክስ ለፍርድ ቤት የሚያቀርብበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ በተጨማሪም የማህበራት መፍረስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች ማህበራት በአባላቱ ፈቃደኝነት/ውሳኔ የሚፈርሱባቸውን ሁኔታዎች/voluntary dissolution/ እና በአስገዳጅ ሁኔታ መፍረስን /involuntary dissolution/ መለየትና ተገቢውን ድንጋጌዎች ማካተት አለበት ፡፡ ስለንብረት ማጣራትም ዘርዘር ያሉ ድንጋጌዎች ቢያካትት የተሻለ ነው ፡፡

**ክፍል አስር:- ሕዝባዊ መዋጮ**

**40. ሕዝባዊ መዋጮ ስለመከልከል (አንቀጽ 112 እና 113)**

እነዚህ አንቀጾች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ህዝባዊ መዋጮ ለመሰብሰብ ፈቃድ ስለሚከለከሉበት ሁኔታ ይደነግጋሉ። ፈቃድ ለመከልከል ከተቀመጡት ምክንያቶች በተጨማሪ በአንቀጽ 112/2 ኤጀንሲው አስፈላጊ መስሎ ሲያገኘው ሌሎች የክልከላ ምክንያቶችን በመመሪያ ለማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል። ይህም ኤጀንሲው የራሱን የመከልከል ስልጣን የሚወስንበት አግባብ ያልሆነ ሁኔታን ይፈጥራል። በአንቀጽ 113/1ሐ ደግሞ ኤጀንሲው የሰጠውን ያልተገለጸ ትዕዛዝ መተላለፍ ለክልከላና ገደብ ምክንያት ሆኖ ተቀምጧል።

እነዚህ እና ሌሎቹም የክልከላ ምክንያቶች ግልጽ የሆነ መለኪያ ሳያስቀምጡ ለኤጀንሲው ሰፊ ስልጣን የሚሰጡ ሆነው ይታያሉ። ኤጀንሲው በሌሎች አንቀጾች የተሰጡትን የፋይናንስ ቁጥጥር ሥልጣናት ስንመለከት ደግሞ የነዚህ ክልከላዎች አስፈላጊነታቸው አጠራጣሪ ይሆናል። በውጤቱም ሕዝባዊ መዋጮ በኤጀንሲው መልካም ፈቃድ ላይ ብቻ የተመሰረተ ጉዳይ ያስመስለዋል። ይህ ደግሞ በተለይ ቢያንስ 90 በመቶ የሚሆነውን ገቢያቸውን ከአገር ውስጥ እንዲሰበስቡ በአዋጁ የሚጠበቅባቸውን ኢትዮጵያውያን ድርጅቶች እና ማህበራት በየአቅጣጫው ገቢ የሚያሳጣ ውጤት ሊኖረው ይችላል።

> **የማሻሻያ ሀሳብ:-** በመጀመሪያ ሕዝባዊ መዋጮ መጠየቅና መሰብሰብ ለበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት መብት ሆኖ በመርህ ደረጃ ቢቀመጥ ይመረጣል። ለዚህ መብት አፈፃፀም ድንጋጌዎችን ማውጣት የሚያስፈልግ ሆኖ ከተገኘም ቢያንስ አጠቃላይ ድንጋጌዎች መውጣት ያለባቸው በአዋጅ መሆን ይገባዋል። የኤጀንሲው መመሪያ የማውጣት ስልጣን አስፈላጊ ከሆነ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም እንጂ አዲስ መብት፣ ግዴታና ገደብ ለመፍጠር መሆን የለበትም። በተጨማሪም በነዚህ ድንጋጌዎች መሰረት በኤጀንሲው የሚሰጡ ውሳኔዎች በአስተዳደር ሥነ-ሥርዓትም ሆነ ይህ ከተጠናቀቀ በኋላም በፍርድ ቤት የሚከለሱበት አግባብ መቀመጡ አስፈላጊ ነው።

**ክፍል አስራ አንድ:- የገቢ ግብር**

**41. ከገቢ ግብር ነፃ ስለማድረግና የገቢ ማስገኛ ስራዎች (አንቀጽ 114 እና 115)**

እነዚህ አንቀጾች በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ከገቢ ግብር ነጻ የሚሆኑበትን እና የገቢ ማስገኛ ስራዎች የሚሰሩበትን አግባብ ለመጀመሪያ ጊዜ በህግ የሚወስኑ በመሆናቸው የረቂቅ አዋጁ ዋነኛ ጠንካራ ጎኖች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው። ሆኖም ግን በረቂቅ አዋጁ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ነፃ የተደረጉት ከገቢ ግብር ብቻ ነው። ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት የፋይናንስ አቅም ዘላቂነት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች የታክስ አይነቶችን በተመለከተ ለምሳሌ ለሲቪል ማህበረሰብ ተቋማት እርዳታ ለሚሰጡ የአገር ውስጥ የንግድ ድርጅቶችና ግለሰቦች የግብር ቅነሳ **(tax deductions for people who make donations to CSOs)**፣ በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ከሚከፈሉ ግብሮችና ክፍያዎች ነፃ መደረግ፣ ከውጭ በሚገቡ እቃዎች ላይ ከሚከፈል የጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመደረግ፣ ከተጨማሪ

እሴት ታክስ ክፍያ ነፃ የመደረግና የመሳሰሉትን በተመለከተ በረቂቅ አዋጁ ምንም የተካተተ ነገር የለም።

በአንቀጽ 114/3 አባባል የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ከሁሉም የገቢ ግብር ነጻ ሲሆኑ ማህበራት ግን ከገቢ ግብር ነጻ የሚሆኑት ከአባላት የሚገኝ መዋጮን በተመለከተ ብቻ ይሆናል። እንደሚታወቀው በአገራችን የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት በተመሣሣይ ተግባራት ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው በዚህ አንቀጽ በበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና በማህበራት መካከል የተደረገው የገቢ ግብር ግዴታ ልዩነት በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ አይደለም። እንደሚታወቀው የአባላት መዋጮ የአብዛኞቹን ማህበራት ጠቅላላ ገቢ ጥቂት ክፍል ብቻ የሚሸፍን እንደመሆኑ የዚህ ንኡስ አንቀጽ ውጤቱ የሲቪል ማህበራትን የፋይናንስ አቅም ማዳከምና ህልውናቸውንም ማሳጣት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም ማህበራትን ከማቋቋም ይልቅ ወደ ደርጅት መዋቅር ዜጎችን የመግፋት አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደር የመደራጀትን ተነሳሽነት ሊያዳክም ይችላል። ከዚህ ጎንም ለጋሾች ከማህበራት ይልቅ ለድርጅቶች መስገስ እንዲመርጡ የሚያደርግም ይሆናል። ከፍትሃዊነት አኳያም ቢሆን ሁለት ተቋማት ለተመሳሳይ ዓላማ ምንአልባትም ከአንድ ምንጭ የሰበሰቡትን ገቢ በዚህ መልኩ ለይቶ ማስገበር አግባብነት ያለው አይመስልም።

> *የማሻሻያ ሀሳብ፡- ከመደራጀት መብት መሰረታዊ ባህሪ እና ከሌሎችም የፖሊሲ ታሳቢዎች አንጻር ለበጎ አድራጎት ስራ የሚሰጡት ከግብር ነጻ የመሆን መብቶች መስፋትና ለሁሉም ማህበራትና ድርጅቶች ያለልዩነት ቢቀመጡ አግባብነት ይኖረዋል። መንግስት በድህነት ቅነሳ እቅዶቹ የሲቪል ማህበራት የልማት አጋሮቹ እንደሆኑ የገለጸውን ወደ ተግባር በመቀየር የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንም ሆነ ማህበራትን ከገቢ ግብር፣ ከውጭ በሚገቡ እቃዎች ላይ ከሚጣል ቀረጥና ቀጥተኛ ካልሆኑ ታክሶች ነጻ እንዲሆኑ ማድረጉ የተሻለ ይሆናል።*
>
> *ከመደራጀት መብት መሰረታዊ ባህሪ እና ከሌሎችም የፖሊሲ ታሳቢዎች በመነሳት የነዚህ አንቀጾች ይዘት በተለይም ማህበራትን በሚያበረታታ፤ ቢያንስ በአጭር ጊዜም ቢሆን በማያዳክም መልኩ እንደገና ሊታይ ይገባል።*

**ክፍል አስራ ሁለት፡- ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**42. የወንጀል ድርጊቶች (አንቀጽ 116)**

ይህ በአድና ማህበራት ከመተዳደሪያ ደንባቸውና ከረቂቁ ህግ ወሰኖች ውጪ ሰርተው ቢገኙ በመቀጮ ወይም/እና በቀላል እስራት እንደሚቀጡ ይደነግጋል። ማህበራት እና በአድ በመተዳደሪያ ደንባቸው ከተገለጹት አላማዎች ውጪ ሌሎች ስራዎች ማከናወናቸው ስህተት ቢሆንም ያከናወኗቸው ስራዎች በራሳቸው ህጋዊ እስከሆኑ ድረስ እንደወንጀል ሊቆጠሩ እና ከባድ ቅጣት ሊጣልባቸው አይገባም። ለምሳሌ በጤና ዘርፍ ብቻ መሰማራትን አላማው አድርጎ የተቋቋመ በአድ ከመተዳደሪያ ደንቡ ውጪ በትምህርት ወይም በባህል ዘርፍ ሲሰራ ቢገኝ መተዳደሪያ ደንቡን መጣሱ ስህተት ቢሆንም ስራው ግን ለህዝብ ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ ወንጀል አያሰኘውም፡ ለከባድ ቅጣትም ሊዳርገው አይገባም። ይልቁንም ይህ አስተዳደራዊ ጥፋት መሆኑ ታውቆ በማስጠንቀቂያ ወይም በገንዘብ ቅጣት ሊታረም

እና ድርጅቱም የመተዳደሪያ ደንቡን እንዲያሻሽል በማድረግ ሁኔታውን ቢያስተካከል የተሻለ ይሆናል፡፡

**42. አቤቱታና ይግባኝ (አንቀጽ 118)**

ይህ አንቀጽ ኤጀንሲው የሚቀርቡለትን ጉዳዮች በተገቢው አጭር ጊዜ ውስጥ መወሰን እንዳለበት የሚደነግግ ቢሆንም የተገቢው ጊዜ ርዝመት ለኤጀንሲው ለራሱ የተተወ ይመስላል፡፡ በአንጻሩ በኤጀንሲው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን በመጀመሪያ ለሚኒስትሩ ቀጥሎም ለፍርድ ቤት አቤት የሚልበት የግዜ ገደብ በ15 ቀናት ተወስኗል፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ በጣም አጭር ከመሆኑ በተጨማሪ ወደ ፍርድ ቤት አቤት ማለት የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ብቻ እና እነርሱም ቢሆኑ የህግ ጥያቄን ብቻ በተመለከተ ይሆናል፡፡ በፍትሐ ብሔር ስነ ስርዓት ህጉ እንኳን ለይግባኝ የሚሰጠው ጊዜ ሁለት ወር ሲሆን በዜግነት ምክንያትም ልዩነት አይደረግም፡፡ ይህም ማለት የፍሬ ነገር ጉዳይን በተመለከተ በሚኒስትሩ የሚሰጥ ውሳኔ በፍርድ ቤት በድጋሚ ሊታይ አይችልም ማለት ነው፡፡ በኤጀንሲው እና በሚኒስትሩ ውሳኔዎች ላይ የግዜ ገደብ አለመኖሩን በተለይ በምዝገባ ጉዳይ አሉታዊ ውጤት የሚያከብደው ደግሞ በንኡስ አንቀጽ 4 ስር በይግባኝ ሂደቱ መጀመሪያ የተሰጠው ውሳኔ ተፈጻሚ ሆኖ የሚካሄድ መሆኑ ነው፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** ከዚህ በላይ በተደጋጋሚ እንደተገለጸው መሰረታዊ መብቶችን የተመለከተ የአስተዳደር ውሳኔ በፍርድ ሂደት የሚከለስ መሆኑ ከህገመንግስቱ፣ ከአለም አቀፍ ስምምነቶች፣ ከህግ የበላይነት እና ከፍርድ ቤቶች የስልጣን ነጻነት አንጻር የግድ ሊሆን የሚገባ ነው፡፡ በተለይም ለኤጀንሲው እና ለሚኒስትሩ ከተሰጣቸው እጅግ ሰፊ ስልጣን አኳያ የፍርድ ቤቶች ሚና ከፍተኛ ሊሆን ይገባል፡፡ በመሆኑም በህግ ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን በፍሬ ነገር ላይም ሁሉም ማህበራት እና በአድ ይግባኝ የማቅረብ መብታቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ለይግባኝም የተሰጠው ጊዜም በቂ ስላልሆነ ቢራዘም /ቢያንስ ከፍርድ ቤት ውሳኔዎች ይግባኝ ለማለት ከሚሰጠው ጊዜ ጋር የተመጣጠነ ቢሆን/ የተሻለ ነው፡፡

**43. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች (አንቀጽ 124)**

የዚህ የመሸጋገሪያ አንቀጽ ድንጋጌዎች አዋጁ ተፈፃሚ ከሆነበት ቀን አንስቶ በአንድ አመት ውስጥ ቀደም ሲል ተመዝግበው የነበሩ ድርጅቶችና ማህበራት በድጋሚ እንዲመዘገቡ ያስገድዳል፡፡ ይህም ማለት በተለይም ኢትዮጵያዊ ሆነው ለመቀጠል የሚፈልጉ ድርጅቶች እና ማህበራት የገቢ ምንጫቸውን፣ የማህበራትን አባላት ቁጥር፣ መዋቅራቸውን፣ አሰራራቸውን በአጠቃላይ ባህሪያቸውን መቀየር ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምንም እንኳን የአንድ አመት ጊዜ መሰጠቱ የሚጠቅም ቢሆንም በተለይ ከማህበራት ባህሪ አንፃር አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ በቂ ጊዜ አይደለም፡፡ በሌላ አባባል አሁን ያሉት አገር በቀል ድርጅቶች እና ማህበራት ወይ ይፈርሳሉ አልያም ህገወጥ ተደርገው ይታያሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከአዋጁ የተገለጸ ዓላማም ሆነ በስራ ላይ ካሉ ፖሊሲዎች መንፈስ ጋር የሚቃረን መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ለመንግስትም ቢሆን በአዋጁ የተጠቀሱትን አካላት ለማቋቋም እና አቅማቸውን በሚገባ ለማደራጀት በቂ ጊዜ የሚሆን አይመስለንም፡፡

> **የማሻሻያ ሀሳብ፡-** የመሸጋገሪያው ጊዜ የማህበራቱን ህልውና ለማስጠበቅ በሚያስችል መልኩ ቢራዘም የተሻለ ነው፡፡